# አዲስ ዘመን

ኢፕድ
ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 135 ጥር 15 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

# የፈረስ ትርኢት ማሳያ ማዕከል ለመገንባት ጥረቶች መጀመራቸውን የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ

## 83ኛውን የአገው ፈረሰኞች በዓል ለማክበር ዝግጅት ተጠናቅቋል

**ጸጋዬ ጥላሁን**

እንጅባራ፡- የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ከእንጅባራ ከተማ አስተዳደር ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ የፈረስ ትርኢት የሚታይበት የፈረስ ፌስቲቫል ትርኢት ማሳያ ማዕከል ለመገንባት ጥረቶች መጀመራቸውን የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ጋርዳቸው ወርቁ ገለጹ።

የአዊ ብሔረሰብ ዞን፣ የአገው ፈረሰኞች ማህበርና የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የ83ኛው በዓል ዝግጅትን አስመልክቶ የጋራ መግለጫ ሰጥተዋል።

ዶክተር ጋረዳቸው ወርቁ እንደገለፁት፤ የአገው ፈረሰኞች ማህበር ለአባላቱ እና ለአካባቢው ማህበረሰብ ከሚሰጠው ማህበራዊ እና ታሪካዊ ፋይዳው ባሻገር አገሪቱን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንድትሆን የፈረስ ፌስቲቫል ትርኢት ማሳያ ማዕከል ለመገንባት ጥረቶች መጀመራቸውን ተናግረዋል።

የአገው ሕዝብ ገናና ታሪኩ በጥንት በኪነ ህንፃው፣ በአገር በቀል እውቀቱ፣ በሕግ አክባሪነቱ እና በታታሪነቱ የሚታወቅ ትልቅ ሕዝብ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከዚህ ታሪኩ ባሻገር የአገው ፈረሰኞች ማህበር የአዊ ዞን ሕዝብ ምልክትና መገለጫ ሆኗል፡፡

ኢትዮጵያውያን በሙሉ የአገው ፈረሰኞች ማህበር ሲያስቡት የአገውን ሕዝብ እንደሚያስቡት፣ የአገው ሕዝብን ሲያስቡት የአገው ፈረሰኞች ማህበሩን እንደሚያስቡት ያስረዱት ፕሬዚዳንቱ፤ ሁለቱም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ሆኖ የመጣ ድንቅ ኢትዮጵያዊ ፌስቲቫል እየሆነ ይገኛል።

ከበዓሉ ቀደም ብሎ በተለይም ጥር 21 እና 22 የማህበሩን ፌስቲቫል የሚያጎለብቱ የተለያዩ ፕሮግራሞች

የፈረስ ትርኢት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









## በአገር አቀፍ ደረጃ 70 ከመቶ እናቶች በህክምና ተቋማት የእርግዝና ክትትል ያደርጋሉ

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የቅድመ ወሊድ ክትትላቸውን በህክምና ተቋማት የሚያደርጉ እናቶች 70 ከመቶ መድረሳቸውን የጤና ሚኒስቴር ገለጸ።

በጤና ሚኒስቴር የእናቶች ጤና ፕሮግራም ከፍተኛ

ቤአገር አቀፍ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “አዲሱ የትምህርት ካሪኩለም ለአይነ ስውራን መምህራን በብሬል ሊቀርብ ይገባል“

- የኢትዮጵያ አይነ ስውራን ብሔራዊ ማህበር

## “ካሪኩለሙን በብሬል ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እያደረግኩ ነው”

- የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- አዲሱ የትምህርት ካሪኩለም የመምህራን መምሪያ መጽሐፍ ለአይነ ስውራን መምህራኖች በብሬል ሊዘጋጅ ይገባል ሲል የኢትዮጵያ

አዲሱ የትምህርት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “የኮተቤ መንገድ ግንባታ መዘግየት ለተለያዩ ችግሮች ዳርጎናል”

- የኮተቤ አካባቢ ነዎሪዎችና አሽከርካሪዎች

## “የመንገዱ ግንባታ በየካቲት ወር መጨረሻ ይጠናቀቃል”

- የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡ የአራራት - ኮተቤ- ካራ የአስፓልት መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በተያዘለት ጊዜ ባለመጠናቀቁ ምክንያት ለከፍተኛ እንግልት እንደዳረጋቸው ነዋሪዎች እና አሽከርካሪዎች ተናገሩ፡፡

"የኮተቤ መንገድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ዜና


ዶክተር ፀጋ ጥበቡ

# በአማራ ክልል በስድስት ወራት 17 ነጥብ 24 ቢሊዮን ብር ገቢ ተሰበሰበ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ግማሽ ዓመት 17 ነጥብ 24 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰብ መቻሉን የአማራ ክልል ገቢዎች ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአማራ ክልል ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ፀጋ ጥበቡ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ ከሰበሰበው የስድስት ወራት ገቢ ውስጥ 15 ነጥብ 24 ቢሊዮን ብሩ የመደበኛ ታክስ ገቢ ሲሆን፤ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚጠጋው ደግሞ የማዘጋጃቤታዊ ግብር ገቢ ነው።

በዘንድሮው ዓመት በአማራ ክልል ከታቀደው 42 ነጥብ 85 ቢሊዮን ብር አጠቃላይ ገቢ ውስጥ 40 ነጥብ 23 በመቶውን ገቢ በስድስት ወራት ውስጥ ማሳካት ተችሏል ብለዋል፡፡

በክልሉ ከ400 ሺህ በላይ ግብር ከፋዮች መኖራቸውን የገለጹት ዶክተር ጸጋ፤ የክልሉ ግማሽ ዓመት ገቢ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ6 ነጥብ 67 ቢሊዮን ብር ጭማሪ ማሳየቱን አስታውቀዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ ገቢው እንዲጨምር የተለያዩ የቁጥጥርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተከናውነዋል። በግብር ከፋዮች ዘንድ የሚስተዋሉ የሥነ ምግባር ጉለቶችን ለማስቀረት በተለያዩ የክልሉ ከተሞች ውይይት ተደርጓል።

በግብር አሰባሰቡ በኩል የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ተከታታይነት ያለው የሥነ ምግባርና የአመለካከት ሥልጠናዎች ለሰራተኞች እንዲሰጡ መደረጉን አስታውቀዋል።

ከዚህ ባለፈ ችግር የተገኘባቸው ሰራተኞች ላይ እርምጃ በመውሰድ ማስተካከያ ተደርጓል። በተለይ ሀሰተኛ ደረሰኝ በመጠቀም ሲያስጭበረብሩ በተገኙ አራት የተቋሙ ሰራተኞች ከሥራ ገበታቸው እንዲነሱ ተደርጎ በፀረ ሙስና ወንጀል እንዲጠየቁ ለማድረግ ጉዳያቸው በፍርድ ሂደት ላይ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም በታክስ ማጭበርበር ላይ የተሰማሩ ዘጠኝ ሰራተኞችን በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ እየተሰራ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ከሰራተኞች ባለፈ በግብር ከፋዩ ላይም የተለያዩ እርምጃዎች መወሰዳቸውን የገለጹት ዶክተር ፀጋ፤ የግብር ከፋዩን ህብረተሰብ ግብርን ከሚሰውርባቸው መንገዶች መካከል ደረሰኝ ያለመቁረጥ፣ በትክክል ገቢን አለማሳወቅና ተያያዥ ችግሮች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

ሀሰተኛ ሪፖርት ባስመዘገቡ የግብር ከፋዮች ላይ በባለሙያዎች ድንገተኛ ቆጠራ በማካሄድ ትክክለኛ መጠናቸውን የማወቅ ስራ ለመስራት ተችሏል። በተደጋጋሚ ጊዜ የህግ ጥሰት የታየባቸው ከ60 በላይ ግብር ከፋዮች 50 ሺህ ብር ቅጣት እንዲጣልባቸውና ጉዳያቸው በሕግ እንዲያዝ ተደርጓል ብለዋል።

በቀጣይ የተሻለ ገቢ ለማግኘት የግብር አሰባሰብ ሥርዓቱን ማዘመን ያስፈልገዋል ያሉት ዶክተር ፀጋ፤ ለግብር ከፋዮች የተቀላጠፈ አገልግሎት በመስጠት ረገድ በቴክኖሎጂ የታገዘ ሥራ መሰራት አለበት ሲሉ አስረድተዋል።

# የሲዳማ ክልል የፀረ ሙስና ኮሚቴ ስራ መጀመሩን አስታወቀ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- አምስት አባላት ያሉት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል የፀረ ሙስና ኮሚቴ የሙስና ማጣራት ስራ መጀመሩን አስታወቀ።

የሲዳማ ክልል የፀረ ሙስና ኮሚቴ ሰብሳቢና የክልሉ ዓቃቤ ሕግ ቢሮ ኃላፊ አቶ ማቶ ማሩ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደለጹት፤ በክልሉ የሚስተዋሉ የሙስና ችግሮች ላይ ከተለያዩ አካላት ጥቆማ በመቀበል የማጣራት ስራ ተጀምሯል።

አምስት አባላት ያሉት የሲዳማ ክልል ፀረ ሙስና ኮሚቴ በፍትህ ቢሮ ኃላፊ የሚመራ ሲሆን፤ የፀረ ሙስና ኮሚሽን ፣ የመልካም አስተዳደር ዘርፍ ፣ የፀጥታና መረጃ ዘርፍ እንዲሁም የፖሊስ ምርመራ ዘርፍ የስራ ኃላፊዎችን በአባልነት ይዟል ብለዋል።

የፀረ ሙስና ኮሚቴ ሰብሳቢው እንዳስታወቁት፤ ኮሚቴው ሶስት ዋና አካላት ያሉት ሲሆን ጥቆማና መረጃ የሚቀበል፣ መረጃውን በመቀበል ምርመራ የሚያካሂድና የምርመራ ውጤቱን ተከትሎ እርምጃ የሚወስድ አካላት እንዳሉት ተናግረዋል።

ኮሚቴው ለስራው የሚያስፈልገውን ቢሮ በማደራጀት፣ የጥቆማ መቀበያ አድራሻዎችን ይፋ በማድረግና ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ዝግጅቶችን ሲያደርግ መቆየቱን ገልጸው፤ አሁን ላይ ዝግጅቶች ተጠናቀው በሙሉ አቅም ወደ ሥራ መግባቱን ጠቁመዋል።




ኮሚቴው ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ሊከተለው የሚገባውን ሕገ-ደንብ አዘጋጅቷል። የፀረ ሙስና ኮሚቴው በሲዳማ ክልል ሙስና በስፋት የሚስተዋልባቸውን ዘርፎች በመለየት የማጣራት ስራዎችን ጀምሯል።

ስራው ሕዝባዊ ተሳትፎ ኖሮት በየደረጃው ያለውን ማህበረሰብ ማሳተፍ እንዲችል ኮሚቴው በትኩረት እየሰራ መሆኑን የፀረ ሙስና ኮሚቴው ሰብሳቢ ተናግረዋል።

ክልሉ በባለፈው ዓመት ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ከ360 በላይ ሰዎችን ተጠያቂ በማድረግ ከሙስና ጋር ተያይዞ ሊባክን የነበረን የአገር ሀብት በማስመለስና ወንጀለኞችንም ተጠያቂ ያደረገ ስራ መከናወኑን አስታውሰው፤ ከአንድ እስከ አስራ ስድስት ዓመት የሚደርስ የእስር ቅጣት የተጣለባቸው መኖራቸውን አስታውቀዋል።

በቀጣይም ለሚከናወኑ የጸረ ሙስና ትግሎች ህብረተሰቡ የተደራጁ መረጃዎችን በመያዝ ጥቆማዎችን እንዲያቀርብ ጥሪ አቅርበዋል።

በተለይም ህብረተሰቡ ከጥላቻና ስሜት ነፃ በሆነ መንገድ ትክክለኛ የሙስና መረጃዎችን ለኮሚቴው በማቅረብ የተለመደ ትብብሩን ሊያጠናክር እንደሚገባም ሰብሳቢው ተናግረዋል።

በሙስና የሚባክነው የሀገር ሀብት ወደ ልማት እንዲዞር ይበልጥ ጥረት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ማቶ፤ የሚመለከተው አካል በሙሉ የሙስናን ጎጂነት በመረዳት ለፀረ-ሙስና ኮሚቴው ስራዎች አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ እንዳለበት አሳስበዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረውን የፀረሙስና ትግል ተከትሎ የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ ሌብነትንና ብልሹ አሠራርን ለመታገል የክልሉ ሕዝብ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግ ጥሪ ማቅረባቸው የሚታወስ ነው።

# ሚሲዮኑ አንድ ሺህ 900 እስረኞችን ወደ አገር አስመለሰ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በታንዛንያ እስር ቤት ውስጥ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን እስረኞች አንድ ሺህ 900 ያህሉን በስድስት ወራት ወደ ሀገር ቤት ማስመለስ መቻሉን በታንዛኒያ የኢትዮጵያ ሚሲዮን አስታወቀ። ሚሲዮኑ ወጣቶች ከስደት ይልቅ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰርቶ መለወጥ እንደሚችሉ መገንዘብ አለባቸው ብሏል።

በታንዛኒያ የኢትዮጵያ ሚሲዮን መሪ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሽብሩ ማሞ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ወራት አንድ ሺህ 900 እስረኞችን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ የተደረገ ሲሆን በአሁኑ ወቅት አምስት ሺህ ኢትዮጵያውያን እስረኞች በታንዛኒያ እስር ቤቶች ይገኛሉ።

በየጊዜው እስረኞችን የማስፈታት እና ወደ አገር ቤት የማስመለስ ሥራ እየተሰራ መሆኑን የገለፁት አምባሳደር ሽብሩ፤ ሆኖም የስደተኞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ተናግረዋል።

ባለፈው ዓመትም በተመሳሳይ በታንዛኒያ በእስር ቤት ከነበሩ እስረኞች በተለያዩ ጊዜያት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ መደረጉን ጠቁመው ነገር ግን የእስረኞች ቁጥር ከመቀነስ ይልቅ እየጨመረ ነው ብለዋል።

በታንዛኒያ ያለው የኢትዮጵያ ሚሲዮን እስረኞች በእስር ቤት ሰብዓዊ መብታቸው እንዲከበር ጥረት ያደርጋል ያሉት ሚሲዮን መሪው፤ ከእስር እንዲለቀቁም ከሚመለከታቸው የአገሪቱ አካላት ጋር በየጊዜው ውይይት እንደሚያደርግ አብራርተዋል። እስረኞች ወደ አገር ቤት ሲመለሱ ወጣቱን እንዲያስተምሩ፣ ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎች ቃለመጠይቅ በማድረግ ግንዛቤ የመፍጠር ስራን እየሰራ መሆኑንም አክለዋል።

እንደ አምባሳደር ሽብሩ ገለፃ፤ በርካታ ወጣቶች ያላቸውን ባጃጅ፣ ሱቅ፣ መሬትና ጋራዥ ጭምር ሸጠው የሚሰደዱ በመሆናቸው ለአገር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ነው። ወጣቶች ከስደት ይልቅ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰርቶ መለወጥ እንደሚቻል መገንዘብ አለባቸው። በስደት የተሳካላቸው ሰዎች መኪና ቤት


አምባሳደር ሽብሩ ማሞ

ሲገዙ የሚመለከቱ ወጣቶች በአጭር ጊዜ ለመክበር በማሰብ ያላቸው ንብረት ሸጠው ይሰደዳሉ፤ ይህ ተገቢ ዓይደለም።

በዚህ ዙሪያ በተለይም ወላጆች፣ የሐይማት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎችና የመንግሥት ኃላፊዎች ተቀናጅተው ሊሰሩ እንደሚገባ የገለጹት አምባሳደሩ፤ የአመለካከት ለውጥ በአንድ ጀንበር የሚመጣ ባለመሆኑ ብዙ ስራ መስራት እንደሚጠበቅም አስረድተዋል።

እንደ አምባሳደር ሽብሩ ማብራሪያ፤ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለማስታገስ ህገወጥ አዘዋዋሪዎችን አድኖ በመያዝ ለፍትህ ማቅረብ አንዱ መፍትሄ ነው። በኢትዮጵያና በኬንያ ድንበር ላይ ከፍተኛ ስራ መስራትና ለወጣቶች የሚሆን የስራ ዕድል መፍጠር ያስፈልጋል።

ዜጎች ከኢትዮጵያ በኬንያ- ታንዛኒያ አድርገው ደቡብ አፍሪካ ለመግባት በሚጓዙበት ጊዜ በርካታ አገራትን ለማቆራረጥ በኮንቲነር ውስጥ እንደሚጫኑ ገልጸው፤ ደቡብ አፍሪካ ለመግባት በሚደረገው የሕገወጥ ጉዞ በውሃ መወሰድ፣ በአውሬ መበላት፣ በጸጥታ ኃይሎች ተይዘው ለእስር ቤት እንደሚዳረጉም አብራርተዋል።

# በኦሮሚያ ክልል ከ11 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመትና ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ ሰዎች የሚሳተፉበት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ይተገበራል

## ሦስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዷል

**ገመቹ ከድር**



አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ከ11 ቢሊዮን ብር በላይ በሚገመትና ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ ሰዎች የሚሳተፉበት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ እንደሚተገበር የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡ ሥራው በተደጋጋሚ ድርቅ የሚከሰትባቸው አካባቢዎች እና ለታላቁ ህዳሴ ግድብ አስተዋፅዖ በሚያበረክቱ ወንዞች እና ተፋሰሶች ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራ ተጠቁሟል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊና የተፈጥሮ ሀብት ኃላፊ አቶ ኤልያስ ከድር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከጥር 15 እስከ የካትቲ 15 2015 ዓ.ም ድረስ የአፈር እና ውሃ ጥበቃ ሥራ በክልሉ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህም አፈር እና ውሃ ጥበቃ በሚያስፈልግባቸው ስድስት ሺህ 495 ቦታዎች ነው የልማት ሥራው የሚከናወነው፡፡

በአጠቃላይም ከ11 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመትና ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ ሰዎች የሚሳተፉበት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራው ተግባራዊ ይሆናል፡፡

የአካባቢውን የአየር ፀባይ መሰረት በማድረግ ከታህሳስ አንድ ጀምሮ ልማቱ በተወሰኑ ዞኖች ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን ክልሉ መርሃ ግብሩን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረጉን አቶ ኤልያስ ገልጸዋል ፡፡

እንደ አቶ ኤልያስ ገለፃ፣ ሥርዓቱን ባልተከተለ አፈር እና ውሃ አጠቃቀም ምክንያት ለ13 ዓመታት ደርቆ የቆየውን ሀሮማያ ሐይቅ ላለፉት ዓመታት በተሠራው የተቀናጀ የአፈር እና ውሃ ጥበቃ ሥራ ወደ ነበረበት እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ሐይቁ ለቱሪዝም መስህብነት፣ ወጣቶች ተደራጅተው ዓሣ ማስገር እና መዝናኛ ሥራዎችን በመሥራት የሥራ ዕድል በመፍጠር አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ ከአንድ ሺህ በላይ ውሃ ፓምፖች በየቀኑ ለበጋ ስንዴ፣ ለጫት፣ ለአትክልት እና ፍራፍሬ ልማት በመሰስና እንዲለማ እያስቻለ ይገኛል፡፡

ይህንን ምክንያት በማድረግ ከሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባባር ከወረዳ እና ከዞን ለተውጣጡ አንድ ሺህ 900 ግብርና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና እንዲወስዱ መደረጉንና በተቀናጀ የአፈር እና ውሃ ጥበቃ ሥራ የደረቁ ወንዞችንና የተራቆቱ መሬቶችን ወደ ነበሩበት ቦታ መመለስ እንደሚቻል መልዕክት የተላለፈበት ሥልጠና ነው ብለዋል ፡፡

ልማቱ በሦስት ነጥብ ሁለት ሄክታር መሬት ላይ ይካሄዳል ያሉት ኃላፊው፤ ተፋሰስ ልማት ሥራውም ድርቅ በተደጋጋሚ በሚያጠቃቸው አካባቢዎች በተለይ ምሥራቅ ሐረርጌና በሌሎችም አካባቢዎች እርጥበትን የሚያቆዩ የመሬት ሥራዎችና መሬትን ከንክኪ የሚከላከሉ እርከኖች እንደሚሠሩ ገልጸዋል፡፡ በመካከለኛው እና ምዕራብ ኦሮሚያ የጎርፍ መገደቢያ እንደሚሠራ እና በተመሳሳይ ሁሉም አካባቢዎች እንደየ አካባቢያዊ ሁኔታቸው እና ያላቸው የአፈር ባህሪይ መሰረት ተደርጎ ሥራው እንደሚሠራም አክለው ተናግረዋል፡፡

የአፈር እና ውሃ ጥበቃ ሥራው ከአረንጓዴ አሻራ ልማት ጋር ስለሚያያዝ የዘንድሮው አረጓዴ አሻራ ከአፈር እና ውሃ ጥበቃ ስራ ጋር ተያይዞ በዜግነት አገልግሎት በመታገዝ ዘጠኝ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሰዎች በሥራው ላይ ይሳተፋሉ፡፡ በ 11 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ተግባራዊ እንደሚደረግ ተገምቷል፡፡

አፈር እና ውሃ ጥበቃ ሥራ ለአየር ንብረት ለውጥ ለመቋቋም ወሳኝ ሥራ ነው ያሉት አቶ ኤልያስ፤ የተጀመሩ ሥራዎችን ከግብ ለማድረስ አረንጓዴ አሻራ ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡ ለአምስተኛ ዙር ለሚካሄደው አረንጓዴ አሻራ ልማት አራት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል፡፡ ለዚህም ዝግጅት እስከ አሁን ድረስ በተሰራው ስራ 1 ነጥብ 8 ቢሊዮን ችግኞች ተዘጋጅተዋል፡፡

አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ፣ በየደረጃው የሚገኙ ባለሙያዎች በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ተግባራዊ እንዲያደርጉ አቶ ኤልያስ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ሳልተገደበ ጊዜ ይሰጣል

## ተፈታኞች ወጪውን ተጋርተው መውጫ ፈተናውን ይወስዳሉ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አዲስ አበባ፡- የተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ላልተገደበ ጊዜ እንደሚሰጥ ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና ብቃት ማሻሻያ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሰይድ መሀመድ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት፤ ተማሪዎቹ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሚያገኙት ፈተናውን ወስደው ብቁ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው። በመሆኑም ፈተናውን ወስደው ማለፍ ያልቻሉ ተማሪዎች ፈተናውን ደጋግመው መውሰድ የሚችሉበት አጋጣሚ ተመቻችቷል ብለዋል።

የዩኒቨርሲቲ ቆይታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች በየስድስት ወሩ ፈተናውን የሚወስዱበት ዕድል እንዳለ የጠቆሙት አቶ ሰይድ፤ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ የህክምና ተማሪዎችና አንዳንድ የትምህርት ክፍሎች ተማሪዎቻቸውን የሚያስመርቁት እንደብዙዎቹ የትምህርት ክፍሎች ሰኔ ላይ ባለመሆኑ ነው ብለዋል።

የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ተመራቂዎች ተማሪዎች ለአንድ ጊዜ ብቻ የፈተና ወጪያቸው እንደሚሸፈንላቸው ያነሱት አቶ ሰይድ፤ ከዚያ ውጪ ለሚያደርጉት ፈተና ለአንድ ተማሪ የወጣው ወጪ ተሰልቶ ተፈታኝ ተማሪዎች ራሳቸው ወጪውን በመሸፈን እንደሚፈተኑ ተናግረዋል።

አሁን ባለው መረጃ ተለዋዋጭነት ሊኖረው ቢችልም የተፈታኞቹ ቁጥር በመንግሥት 146 ሺህ እንዲሁም ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት 110 ሺህ በድምሩ 256 ሺህ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና እንደሚወስዱ የገለጹት አቶ ሰይድ፤ ለእነዚህ ተፈታኞች በዩኒቨርሲቲዎች ያለውን የኮምፒዩተር አቅርቦት እና የተፈታኞች ብዛት በመለየት የመውጫ ፈተናውን በኦንላይን ለመስጠት ዝግጅት መደረጉን ጠቁመዋል። የኮምፒውተርና የመፈተኛ ተቋማት ልየታም ተደርጓል ብለዋል።



ፎቶ - በገባቦ ገብሬ

አቶ ሰይድ መሀመድ

አራት የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ጨምሮ በአጠቃላይ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችን በመውሰድ 33 ሺህ የሚሆኑ ኮምፒውተሮች ዝግጁ ናቸው ያሉት አቶ ሰይድ፤ በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች አካባቢ ችግር እንዳያጋጥም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እንደሚሰሩም ተናግረዋል።

እንደ አቶ ሰይድ ገለጻ፤ በመንግሥትና በግል ተቋማት ላይ የሚሰጡ ከ300 በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ፕሮግራሞች አሉ። ሁሉንም ተማሪ በአንድ ጊዜ መፈተን አይጠበቅምና በየትምህርት መስኩ እየተደረገ በአስር ዙር ፈተናው ለመስጠት ታቅዷል። በአንድ ቀን ውስጥም 30 የትምህርት ክፍሎችን ለመፈተን ታስቧል።

# "የሰላም ስምምነቱ በግጭት አካባቢ የነበሩ ተቋማትን በትክክለኛው መንገድ ኦዲት ለማድረግ ያግዛል"

- አቶ አበራ ታደሰ

የፌዴራል ኦዲተር መስሪያ ቤት ምክትል ዋና ኦዲተር

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበበ ፡- በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተደረሰው የሰላም ስምምነት በጦርነቱ አካባቢ የነበሩ ተቋማትን በትክክለኛው መንገድ ኦዲት ለማድረግ ያግዛል ሲሉ የፌዴራል ኦዲተር መስሪያ ቤት ምክትል ዋና ኦዲተር አቶ አበራ ታደሰ ገለጹ።



አቶ አበራ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በሰላም ስምምነቱ ትግበራ ምክንያት በጦርነት አካባቢ የነበሩ ተቋማት ላይ የኦዲት ስራዎችን ማከናወን የሚያስችል አውድ እየተፈጠረ ይገኛል።

በጦርነቱ ወቅት የተለያዩ የፌዴራል ተቋማት ኦዲት ለማድረግ እንዳልተቻለ አቶ አበራ ጠቁመው፤ ለአብነትም መቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ፣ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲና ደሴ የሚገኙ የተለያዩ ተቋማት እንዲሁም ሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ለማድረግ አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጥሮ እንደነበር አስታውሰዋል።

በዚህ ምክንያት የአንዳንድ ተቋማትን ስራ ኦዲት ለማድረግ ተጨማሪ ወጪ ይወጣ ነበር፤ ለአብነት የመቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲን ኦዲት ለማድረግ ጎንደር ድረስ ሰነዳቸውን እንዲያመጡ ተደርጎ ሲሰራ እንደነበር ተናግረዋል።

ችግሩ ተፈትቶ ሰላም በመሆኑ የፌዴራል ኦዲተር መስሪያ ቤትን ስራ ለማከናወን መልካም አጋጣሚ ተፈጥሯል። እስካሁን የኦዲት ስራቸው ተቋርጦ የቆዩባቸውን ተቋማት ዳግም ኦዲት ለማድረግ ዝግጅት ተደርጓል ሲሉ አቶ አበራ አስታውቀዋል።

በጦርነቱ ምክንያት የተጎዱት ዩኒቨርሲቲዎች ላይ የሚደረጉ ድጋፎች ይኖራሉ ነገር ግን የተደረገው ድጋፍ በትክክል መድረሱን አለመድረሱን የማጣራት እንዲሁም ወደ መደበኛ ስራቸው ሲመለሱ የኦዲት ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ማድረግ አለማድረጋቸው መከታተል ስለሚጠበቅብን ለኦዲት ስራው ዝግጁ ሆነን እየሰራን እንገኛል ብለዋል።

ከተቋማት የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ጋር ተያይዞ ስህተቶች አሊያም የመረጃ መጥፋት ሊከሰት ስለሚችል በኦዲት ሥርዓቱ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል ያሉት አቶ አበራ፤ በተቻለ መጠን ተጣርተው በሚቀርቡ ማስረጃዎች ላይ በመመርኮዝ አስፈላጊው የኦዲት ስራ እንደሚከናወን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል የፌዴራል ዋና ኦዲተር በክልሎች በተለያየ ጊዜ የሚከሰተው የጸጥታ ችግር ሰራተኞቹ በተፈለገው ጊዜ ተንቀሳቅሰው እንዳይሰሩ እክል ፈጥሯል። ይህ ችግር ተወግዶ በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ አማራ፣ አፋርና ትግራይ ክልልች ሰላም በመውረዱ በርካታ የፌዴራል ተቋማት በቀጣይ የክዋኔ ኦዲታቸው እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል የፌዴራል ዋና ኦዲተር በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት ከፋይናንስ ኦዲት በተጨማሪ 5 የልዩና 25 የክዋኔ ኦዲት ስራዎችን እያከናወነ መሆኑን ተናግረዋል። የተቋማት የኦዲት ግኝት ሪፖርትም እስከ ጥር 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ተጠናቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሚቀርብ ጠቁመዋል።

ዜና

# ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የተሰጠ መግለጫ

መግለጫውን የሠጡት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት እና ብፁዕ አቡነ አብርሃም የጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ አኪያጅና የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፣ በመንበረ ፓትርያርክ የተገኙ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ናቸው።

ቅዱስነታቸው በትናንትናው ዕለት በተሰማው ሕገ ወጥ "ሢመተ ጳጳሳት" ጉዳይ በሰጡት መግለጫ ጉዳዩ ከቅዱስ ሲኖዶስ እውቅና ውጪ በሕገወጥነት የተከናወነ መሆኑን በመግለጽ:-

1. በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ያሉ ሊቃነ ጳጳሳት በአስቸኳይ ወደ መንበረ ፓትርያርክ እንዲመጡ ጥሪ ቀርቧል።

2. መንግሥት ክስተቱ በአገር ላይ ጭምር የሚያስከትለውን ጉዳት ተመልክቶ በጉዳዩ ላይ ሕጋዊ ሃላፊነቱን እንዲወጣ ጥሪ ቀርቧል።

3. ምዕመናን ቤተክርስቲያንን ከመቸውም ጊዜ በላይ በንቃት እንዲጠብቁ ቅዱስነታቸው ጥሪ አቅርበዋል።

## "አዲሱ የትምህርት ካሪኩለም....

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አይነ ስውራን ብሔራዊ ማህበር ጠየቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በበኩሉ ካሪኩለሙን በብሬል ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እያደረገ መሆኑን አስታውቋል።

የኢትዮትጵያ ዓይነ ሰውራን ብሔራዊ ማህበር አካቶ ትምህርት ኃላፊ አቶ ከተማ ገብሬ የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት መጽሐፍ ለአይነ ስውራን መምህራንም ሆነ ተማሪዎች በብሬል ባለመቅረቡ የትምህርት ሂደቱ ላይ ችግር መፍጠሩን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል።

አቶ ከተማ እንዳስታወቁት፤ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ካሪኩለም ሲቀይርና መጽሐፎች ሲያሻሽል ዓይነ ስውራን በብሬል የሚያገኙበት ሁኔታ ታሳቢ የሚያደርገው ከረጅም ጊዜ ቆይታ በኋላ ነው።

በችግሩ የተነሳ ዓይነ ስውራን ተማሪዎችና መምህራን በራሳቸው ወጪ መጽሐፍትን ወደ ብሬል በማስገልበጥ በተደጋጋሚ ለአላስፈላጊ ወጪና እንግልት ይዳረጋሉ ብለዋል፡፡

ትምህርት ቢሮ የአዲሱ ካሪኩለም መጽሐፍት ለመምህራኖች በሶፍት ኮፒ ሲሰጥ ለዓይነ ስውራን መምህራኖችም ሊጠቀሙበት በማይችሉት መንገድ አብሮ በሶፍት ኮፒ መስጠቱን ተናግረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት መምህራን ወደ ማህበሩ በመምጣት ወደ ብሬል እንዲገለበጥላቸው ጠይቀዋል ሲሉ አስረድተዋል።

ማህበሩ ትክክለኛውን ሶፍት ኮፒ ከትምህርት ቢሮ ባለማግኘቱ ከመምህራን የተሳሳተ ሶፍት ኮፒ ተቀብሎ በማተሙ በተደጋጋሚ ለኪሳራ መዳረጉን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ከዚህ በፊት በነበሩ የብሬል መማሪያ መጽሐፎች ላይ የፊደልና ግድፈት እንዲሁም የተዘለሉ ገፆች በመኖራቸው በርካታ ዓይነስውራን ቅሬታችውን ለማህበሩ እንደሚያቀርቡ አቶ ከተማ ጠቁመዋል።

ችግሩ የሚከሰተው ብሬል ሲታተም በጨረታ ያሸነፈ ማንኛውም አካል እንዲያትመው በመፈቀዱ ምክንያት ነው። በመሆኑም በቀጣይ ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይከሰቱ ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

ማህበሩ ለዓይነ ስውራን የሚሰራ ለትርፍ ያልተቋቋመ በህግ ሊጠየቅ የሚችል ድርጅት መሆኑን በመረዳት ትምህርት ቢሮ ሥራውን ከማኅበሩ ጋር በትብብር ሊያከናውን ይገባል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በበኩሉ ካሪኩለሙን በብሬል አሳትሞ ለማከፋፈል እየሰራ መሆኑን አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የልዩ ፍላጎት አካቶ ትምህርት ባለሙያው አቶ ዳንኤል አሰራት እንደገለጹት የአዲሱ ሥርዓት ትምህርት ዝግጅት አስመልክቶ በብሬል ለማድረስ ብዙ አማራጮች ተይዘዋል።

የብሬል ህትመት ስራ ጊዜ የሚውስድ መሆኑና የብሬል ማባዣ ማሽን በቀላሉ አለመገኘቱ ለስራው መዘግየቱ ምክንያት መሆኑን ገልጸው በተቻለው ፍጥነት ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ዓይነስውራን ብሔራዊ ማኅበር በሰዓት ከአምስት ሺህ በላይ ገጽ የብሬል ህትመት የሚሰራ ዘመናዊ ማሽን ቢኖውም ይህ ስራ በተለየ መልኩ ህትመቱ ለማህበሩ እንዲሰጠው የሚያዝ መመሪያ የለም። በመሆኑም የብሬል ህትመቱን ስራ በጨረታ ሕጉ መሰረት እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

ትምህርት ቢሮ ከዚህ በፊት የነበሩ የብሬል ማስተማሪያ መጽሐፍት ክፍተት እንደነበረባቸው ተረድቶ በተሻለ ሁኔታ ለማቅረብና ከአይነ ስውራን መምህራን ጋር በጋራ እየሰራ መሆኑ ጠቁመው፤ በጨረታ አሸንፎ የሚያትመውም አካል ህጋዊ አካሄዶችን ተከትሎ በትክክል እንዲሰራ ቁጥጥር እንደሚደረግ አቶ ዳንኤል ገልጸዋል።

## የፈረስ ትርኢት ማሳያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እና ዝግጅቶች ይካሄዳሉ።

የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ በዓሉን በዓለም ቅርስነት በዩኒስኮ እንዲመዘገብ በአገው ጥናት ኢንስቲትዩት በኩል አስፈላጊውን ጥናት በማካሄድ በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

የአዊ ብሔረሰብ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ እንግዳ ዳኛው በበኩላቸው፤ የአገው ፈረሰኞች ማህበር የሁሉም በዓል በመሆኑ በዩኔስኮ እንዲመዘገብ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የራሱን ድርሻ እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

የአገው ፈረሰኞች ማህበር በዓልን በዩኒስኮ ለማስመዝገብ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። በአገር ውስጥ እና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በበዓሉ እንዲታደሙ ጥሪ ተላልፏል። በዓሉ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የሚመለከታቸው እና የጋራ በመሆኑ የአካባቢያችን፣ የአገራችንና ዓለም አቀፍ ቅርስ እንዲሆን ሁሉም ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ አሳስበዋል።

ዘንድሮ ለሚከበረው 83ኛ የአገው ፈረሰኞች በዓል በድምቀት ለማክበር ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቁን የማኅበሩ ፕሬዚዳንት አለቃ ጥላዬ አየነው ተናግረዋል፡፡

ከመስከረም አንድ ጀምሮ የተለያዩ ዝግጅቶች ሲደረጉ ቆይተው ተጠናቅቀዋል። በበዓሉ ስድስት አይነት የፈረስ ትርኢቶች ለማቅረብ እንደተዘጋጁም ጠቁመዋል።

የአገው ፈረሰኞች ማህበር ከ83 ዓመት በፊት የአድዋ ጀግኖችንና የፈረሶችን ውለታ ለማስታወስ በጥቂት አባላት የተቋቋመ ማህበር ነው።

የአገው ፈረሰኞች ማህበር በዓል በመጪው ጥር 23 በእንጅባራ ከተማ በድምቀት ይከበራል።

## በአገር አቀፍ ደረጃ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ድርጅት እንደገለፁት፤ ከዚህ በፊት እናቶች በእርግዝና ወቅት እስከ ወሊድ ድረስ አራት ጊዜ ክትትል የሚያደርጉ ሲሆን አሁን ላይ ደግሞ የቅድመ ወሊድ የክትትል ጊዜ ወደ ስምንት ከፍ ብሏል፡፡

ለእናቶች የሚሰጠው የቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት በሁሉም የጤና ተቋማት እየተሰጠ ነው ያሉት ባለሙያዋ፤ ውስንነት የሚታይበት ቢሆንም በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አማካኝነት በጤና ኬላዎችም አገልግሎቱ እየተሰጠ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

የመጀመሪያማን፣ አራተኛውን እና ስምንተኛውን የቅድመ ወሊድ ክትትል እናቶች በሆስፒታሎች እና በጤና ጣቢያዎች እንዲያደርጉ ይፈለጋል ያሉት ወይዘሮ እቴነሽ፣ በዚህም እስከ አራት ድረስ የሚደረገውን የእርግዝና ክትትል የሚያደርጉ እናቶች መጠን በአገር አቀፍ ደረጃ 70 ከመቶ መድረሱን አስረድተዋል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ የእናቶች ግንዛቤ እያደገ እንደሚገኝ እና በጤና እክስቴንሽን ባለሙያዎች በኩል በየወሩ የነፍሰጡር እናቶች ኮንፈረንስ እየተዘጋጀ መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህም የጤና ኤክስቴንሽን እና የጤና ባለሙያው ከጤና ጣቢያው በመሄድ ስለእርግዝና ክትትል፣ ከወሊድ በኋላ ማድረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች ትምህርት ይሰጣሉ ሲሉ ገልፀዋል።

እንደ ወይዘሮ እቴነሽ ገለፃ፣ የጤና ልማት ቡድን በማደራጀት፤ ማኅበረሰቡ ስለ ጤናው እንዲወያይ ይደረጋል። በቡድኑ አማካኝነት የጤና ኤክስቴንሽኖች በአካባቢው ነፍሰ ጡር የሆኑ እናቶችን በመመዝገብ ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ ክትትል እንዲጀምሩ ያደርጋሉ።

ኢትዮጵያ በዓለማችን ከፍተኛ የእናቶች ሞት ከሚመዘገብባቸው አገራት አንዷ መሆኑዋን የጠቀሱት ወይዘሮ እቴነሽ፤ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ በዓለም ዘላቂ ግብ ተብሎ የተቀመጠ አለ። ይህን ግብ በተሻለ ሁኔታ ለማሳካት የተለያዩ ስትራቴጂዎች ተቀርፆ እየተሠራ ነው፡፡

የእናቶችን እና የህፃናትን ጤና ለማጠናከር ጦርነት በነበረባቸው አካባቢዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት እየሠሩ እንደሆነ ገልፀው አንቡላንሶችን እና የተለያዩ ለህክምና አገልግሎት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ወደ ቦታዎች መላኩን፣ የተጎዱ ሆስፒታሎች መገንባታቸውን እና ለጤና ባለሙያዎችም ሥልጠና መሰጠቱን ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም የጤና ሴክተሩን ለማነቃቃት እና ለመደገፍ እንዲመች በማሰብ ያለፈውን ዓመት የጤናማ እናቶች ወርን በአፋር እና አማራ ክልሎች አድርገናል ሲሉ ገልፀዋል።

ወይዘሮ እቴነሽ እንደገለፁት፣ በቀጣይ የእናቶች ጤና አገልግሎትን የተሻለ ለማድረግ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ከነዚህም የአጥቢያ ዙሪያ ትስስር የአቅም ግንባታ ፕሮግራም አንዱ ነው። በዚህም ሆስፒታሎች በዙሪያቸው ላሉ ጤና ጣቢያዎች ሥልጠናዎችንና ግብዓቶችን በመስጠት አቅማቸውን እንዲገነቡ ያደርጋሉ።

የእናቶች ጤና ፕሮግራም የአንድ አካል ሥራ ብቻ አይደለም ያሉት ባለሙያዋ፤ በመሆኑም በመብራት፣ በውሃ፣ በመንገዶችና በመሳሰሉ ዘርፎች ላይ የሚሰሩ አካላት ለእናቶች የሚሰጠውን አገልግሎት የተጠናከረ ለማድረግ ትብብር እንዲያደርጉ ሲሉ አሳስበዋል።

## "የኮተቤ መንገድ ግንባታ መዘግየት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የመንገዱ ግንባታ በየካቲት ወር 2015 ዓ.ም መጨረሻ ተጠናቆ ሙሉ ለሙሉ ለአገልግሎት ክፍት እንደሚሆን የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ኮተቤ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ አስቴር ተሰማና አሸናፊ አባተ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአካባቢው የተጀመረው የመንገዱ ግንባታ ሳይጠናቀቅ ከስድስት ዓመታት በላይ አስቆጥሯል።

ግንባታው በተባለለት ጊዜ አለመጠናቀቁ በተለይ ለአቅመደካሞች፣ ለህጻናት ብሎም አጠቃላይ ለነዋሪዎች የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ላይ እክል ፈጥሯል። በግንባታው የተነሳ በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ የትራንስፖርት እጥረት በመኖሩ እና ከታሪፍ በላይ እየከፈልን ለመሄድ ተገደናል ብለዋል፡፡

በመንገድ ግንባታው መዘግየት ምክንያት አካባቢያቸው የተሳለጠ የንግድ እንቅስቃሴና ልማት እንዳይኖር አግዷል፡፡ የመንገዱ ግንባታ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ አስፈላጊው ጥረት መደረግ አለበት ሲሉ ነዋሪዎቹ ጠይቀዋል፡፡

ሌላው የአካባቢው ነዋሪና የታክሲ አሽከርካሪ አቶ አቤል ተስፋዬ በበኩሉ የመንገድ ግንባታው መዘግየት በስራውም ሆነ በዕለት ተዕለት ኑሮው ላይ መጥፎ ተፅዕኖ እንደፈጠረበት ተናግሯል።

መንገዱ ተገንብቶ ባለመጠናቀቁ ተሽከርካሪው ጉዳት እየደረሰበት መሆኑን ጠቁሞ፤ ችግሩም የመለዋወጫ ዕቃ እና የጥገና ወጪውን ከፍ እንዳደረገበት ገልጿል።

መንገዱ በ2015 ዓ.ም በተሻለ ሁኔታ እየተገነባ ቢሆንም በተቻለ ፍጥነት በማጠናቀቅ አሽከርካሪዎችንም ሆነ እግረኞችን ከእንግልት ማዳን ይገባል ሲል ሃሳቡን ሰጥቷል።

የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን የራስ ኃይል መንገድ ግንባታ የመንገድ ሶስት ፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ ኢንጂነር ይትባረክ ዘሪሁን በበኩላቸው የመንገዱ ግንባታ ሙሉ ለሙሉ የካቲት 2015 መጨረሻ ላይ ለአገልግሎት ክፍት ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

በተቋራጭነት እየሰራ የነበረው ኮንትራክተር ደካማ የስራ አፈፃፀም በማሳየቱ ውል ተቋርጦ በ2013 ዓ.ም በባለሥልጣኑ የራስ ሃይል መንገዱ እየተሰራ ነው። ግንባታውን በሁለት ዓመታት ለመጨረስ የታቀደ ቢሆንም ከህብረተሰቡ በመጣ የዲዛይን ቅሬታ ፣ የወሰን ማስከበር ፣ የመብራት፣ የስልክ እና ከፍተኛ የውሃ መስመሮችን ለማዘዋወር ጊዜ እንደወሰደ ገልጸዋል።

ችግሮቹን ለመፍታት የዲዛይን ለውጥ በማከናወን ፣ ከአካባቢው አስተዳደር ጋር በመነጋገር የወሰን ማስከበር ችግር የመፍታት ሥራ ተከናውኗል። በተጨማሪም ከመብራት ሃይል እና ከቴሌኮም ጋር በመነጋገር መስመራቸውን ድጋሚ የማስተካከል ስራ እየተከናወነ ይገኛል። ከዚህ ጎን ለጎን አብዛኛው የአስፓልት ንጣፍ ተከናውኗል ብለዋል።

ኢንጂነር ይትባረክ እንደገለጹት፤ የመንገድ ግንባታው አጠቃላይ 2ሺህ 840 ሜትር ርዝመት እንዲሁም 30 ሜትር ስፋት አለው። ከዚህ ውስጥ 2ሺህ 597 ሜትር ወይም 91 በመቶ ተገንብቷል።

ቀሪው የአስፓልት መንገድ ግንባታ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ የሚያስችል ስራ እየተከናወነ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰላም ስምምነቱ ፍሬ መታየትጀምሯል!

ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት ነው። ሰላም ካለ ልማት አለ፤ ኢንቨስትመንት አለ። እንደልብ ተዘዋውሮና ያሻውን ሰርቶ መግባት፣ ነግዶ ማትረፍ ፤ ተምሮ መመረቅ ወዘተ ሁሉንም ነገር ማድረግ ይቻላል። ለአንድ አገር ልማትና እድገት ሰላም ከምንም በላይ ዋጋ አለው፡፡ ለዚህም ነው ሰላም ዋጋው የማይተመን ፣ በምንም አይነት ምድራዊ መመዘኛ የማይሰፈር ለሰው ልጆች እጅግ ወሳኝና አስፈላጊ መሰረታዊ ጉዳይ ነው የሚባለው።

አገር ዋልታና ማገር ቢኖረው ምሰሶው ሰላም ከሌለ ግን እንደ አገር መቆም አይችልም። ህንጻ ቢገነባም ሰላም ከሌለ ይፈርሳል፤ ሕዝቡም ተረጋግቶ አይኖርም፣ ኖሮም አይሰራም ፣ ነግዶም አያተርፍም። ስለዚህ በሁሉም አቅጣጫ ሰላምን ማለምና ስለሰላም መስበክ ይገባል። ያለ ሰላም ምንም ዓይነት ራዕይና ተስፋዎችን ማሳካት አይቻልም፡፡ ከሌሎች አገሮች ለማየት የቻልነውም ይሄንኑ ነው። እነሊቢያ እዚህ ቀረ የማይባል ዘመናዊ ህንጻዎችን በአገራቸው ገንብተው፤ የኢኮኖሚ አቅማቸውን አሳድገው ዜጎቻቸውን ቅንጡ ኑሮን ቢያኖሩም በሰላም መጥፋት ግን ሁሉ ዛሬ ዶግ አመድ ሆኖ ህንጻዎች ወደ ፍርስራሽነት ተቀይረዋል። የመንና ሶሪያም በተመሳሳይ ይሄው እጣ ገጥሟቸው ዜጎቻቸው ለስደት ተዳርገዋል። ይሄ ዛሬ በዓይናችን ያየነው በቅርበት የምናውቀው ክስተት ነው። ልንማርበት የሚገባ ነው። «ብልጥ ልጅ ስህተትን ከሰው ይማራል፤ ሞኝ ደግሞ ከራሱ » የሚል አንድ አባባል አለ። ኢትዮጵያውያን ደግሞ ሁለቱም የመማሪያ እድሎቻችን ከፊታችን ቀርበው አይተናልን። ስለዚህ ከሌላውም ከራሳችንም ስህተት ተምረን ዛሬ ያገኘነውን ሰላም ዘላቂ ለማድረግ መስራት ይጠበቅብናል። አሁን ያገኘነው ሰላም ስንት ወንድሞቻችንን ከሞት ፣ ስንቶቹን ወገኖቻችንን ከመፈናቀልና ከረሃብ እንደታደገ፤ ስንት ለጦርነት ይወጣ የነበረን ፋይናንስ ለልማት እንዳዋለ አይተናል። ስለዚህ ለሰላም ዘብ መቆም ፣ ሰላምን ከምንም ነገር በፊት ማስቀደም ያስፈልገናል።

«ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ» የሚል አንድ የአበው ተረት አለ። አሁን ግን መባል ያለበት ሰላም ካለ በሰማይም መንገድ አለ ነው። ሰላም ከሌለ በየትኛውም አቅጣጫ በየትኛውም የሰማይ ርቀት ላይ መንቀሳቀስም ሆነ ሌሎች የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማድረግ አይቻልም። ስለዚህ ለሰው ልጆች የቅድሚያ ቅድሚያ የሚያስፈልገው ሰላም ነው። ስለዚህ የሀገርን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ ዋነኛው ግዴታና ሃላፊነት የመንግሥት ብቻ መሆን የለበትም፡፡

በፌዴራል መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት መርሆዎች ሙሉ ለሙሉ ተተግብሮ ሳያልቅ እንኳን በአገር ላይ የተገኘው ሰላም ቱሪስቶች ያለ ስጋት ወደ አገራችን እንዲፈሱ አድርጓቸዋል። የውጭ አገር ዲፕሎማቶች አገራችንን መጎብኘት እንዲችሉ ዕድል ሰጥቷቸዋል፤ ሌላም ሌላም። ይሄ የሚያሳየው የሰላም ዋጋ የማይተመን መሆኑንና ስለሰላም ሁሉም ወገን መክፈል የሚገባውን ዋጋና መስዋዕትነት መክፈል እንዳለበት ነው ።

ስራ አጡ ስራ የሚያገኘው ፤ የውጪ ንግድ የሚስፋፋው የአገር ኢኮኖሚ የሚጠገነው ኢንቨስትመንት ሲስፋፋና ባለሀብት በስፋት ኢንቨስት ማድረግ ሲችል ነው። የአገር ውስጡም ሆነ የውጪው ኢንቨስተር ምቹ ሁኔታዎችን ካገኘ ይበልጥ ይሰራል እንጂ አይሸሽም። የሰላም አለመኖር ደግሞ በተቃራኒው ባለሀብትን ያርቃል። ስራአጥ በሀገር ላይ እንዲበረክት ያደርጋል። ወንጀል ይስፋፋል፤ ሙስና፤ ብልሹ አሰራርና የመልካም አስተዳደር ችግሮች አይናቸውን አፍጥጠው ይመጣሉ።

ሰሞኑን በደብርብርሃን ከተማ የተመለከትናቸው ግዙፍ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች የሰላም ውጤቶች ናቸው። ስለዚህ ከሰላም የምናገኘው ትርፍ ሕዝብን ተጠቃሚ አገርን ደግሞ በግለሰብ ደረጃ ግለሰብን በቤተሰብ ደረጃ ቤተሰብን በኅብረተሰብ ደረጃ ኅብረተሰብን እንዲሁም አገርን የሚለውጥ ነውና ትኩረት ልንሰጠው ይገባል።

ለኢንቨስትመንት በተሰጡት መሬቶች ላይ የታቀዱት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀው ወደ ስራ ካልገቡ የአገራችንን መሰረታዊ የኢኮኖሚ ችግሮች መቅረፍ አንችልም፡፡ የኑሮ ውድነትን መለወጥ የሚቻለው በዘላቂነት ምርታማነትን በማሳደግ ነው፡፡ ምርታማነት የሚያድገው ደግሞ የተጀመሩ አምራች የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ወደ ስራ ሲገቡ በመሆኑ ሁሉም አካል በየአካባቢው ያለውን ሰላም አስተማማኝ ማድረግ ይጠበቅበታል!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ፀረ-ሙስና ትግሉ ሥር ነቀል ለውጥ እንዲያመጣ

**ዳንኤል ዘነበ**

ኢትዮጵያ በሙስና ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሷን በመጠቆም፤ በየዓመቱ ቢሊዮኖችን ከሚመዘበሩ ሀገራት መካከል አንዷ ስለመሆኗ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የተሰኘው ተቋም ባለፈው ዓመት ያወጣው መረጃ ያመላክታል። በሀገር ህልውና ላይ የተደቀነው ሙሰኝነት ዛሬም እንደ ትናንቱ ያልተሻገርነው ችግር ሆኗል።

በሃያ ሰባት ዓመቱ የኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት ስርቆት እንደ አንድ የሥራ ዘርፍ ይወደስ ስለነበር ኢትዮጵያዊ የጨዋነት እሴታችንን ፈተና ላይ ጥሎታል፤ ኢኮኖሚያችንን አድቅቆታል፤ ኑሯችንን አመሰቃቅሎታል። በተለይም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰርቶ ሳይሆን ሰርቆ መክበረ እንደዝና መታየት ጀምሯል። የሙስና ተዋናዮቹ ጉዳይ ክብደት እያጣ ፣ተግባሩም ከመጥፎ አተያይ ወደ መልካምነት እየመጣ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን የተጣባቸው ክፉ በሽታ ሆኗል።

በአገሪቱ መረን የለቀቀውን ሌብነት አደብ ለማስያዝ ህግ የማስከበር ዘመቻ መጀምሩ ይታወቃል። ..."ኮሚቴ ተቋቋመ.." ወዘተ የሚሉ ዜናዎች እዚህም እዚያም ይሰማሉ። ጅማሮው ይበል ያሰኛል። በተጀመረው ርምጃ መሠረት መንግሥት ከላይ እስከ ታች የተዘረጋውን የሌብነት ሰንሰለትን መበጣጠስ የሚያስችል እርምጃ ይወስዳል ብዬ እጠብቃለሁ ።

በርግጥ ከመጣንበት መንገድ እና መንገዱ ከፈጠረው ጉራማይሌነት አንጻር የመንግሥት የጸረ-ሙስና ትግል በቀላሉ ስኬታማ ይሆናል የሚል እውነት የለኝም። ከፍያለ ቁርጠኝነትና ጥንቃቄ ጭምር የሚፈልግ ነው።

እንደ ሀገር የተንሰራፋውን ሙስና ለመከላከል ከሁለት አስርተ ዓመታት በፊት ኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን ማቋቋሟ ይታወሳል። ኮሚሽኑ በሁለት አስርተ ዓመታት የተለያዩ ሥራዎችን እንደሠራ ቢገለጽም ሙስናን ከመቀነስ ይልቅ ተንሠራፍቶ የሀገሪቱ ብሔራዊ ስጋት የሆነበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።

የሚገርመው ሌብነት የተንሰራፋውም ሌብነትን የሚዋጋ ተቋም በኮሚሽን ደረጃ የተዋቀረውም በነዚያ ዓመታት ነበር። ሆኖም ሙስና መልኩን እየለዋወጠና እየተንሰራፋ ሲመጣ እንጂ ሲከስም አላየንም። አሁንም ያ ታሪክ እንዳይደገም መጠንቀቅ ያስፈልጋል። የነብርን ጭራ ይዞ መልቀቅ አደጋን ማባባስ ስለሚሆን እስከመጨረሻ መፋለም የግድ ይላል።

ሰሞነኛው የሙስና ዘመቻ በተለያዩ ጊዜያት አጀንዳ ነበር። ታዲያ ዘመቻው ፣ ርብርቡ ፣ ዜናው የአንድ ሰሞን እንጂ ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ያለሙ አልነበሩም። ዛሬ የትናንት ውጤት እንደመሆኑ፤ ለትግሉ ስኬት ከትናንቱ አካሄድ የዛሬን ጅማሮ በአግባቡ መመርመር ያስፈልጋል።

በሀገራችን የነዋሪነት መታወቂያ ከማውጣት፣ የባንክ ብድር እስከመውሰድ ባሉ፤ ከጥቃቅን እስከ ከፍተኛ ደረጃዎች በሚገኙ የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ ሙስና የተለመደ ነው። ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ ፈጥሯል።

መንግሥትም ቢሆን ሀገሪቱ ላይ የሚስተዋለው ሙስና አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን አምኖ ወደ ርምጃ መግባቱን እያሳወቀ ነው። ጉዳዩ እሳት ከማጥፋት ያለፈና ዘላቂ መፍትሄ የሚያመጣ ከሆነ እሰየው የሚያስብል ነው።

የሚወሰደው እርምጃ ትላልቅ አመራሮችን ፣ ሹማምንትን ታሳቢ ያደረገና ከዘመቻ ሥራ በላይ ሥር ነቀል ለውጥ ሊያመጣ የሚችል መሆን ይኖርበታል የሚል የጸና እምነት አለኝ። ይህን ማድረግ ካልተቻለ ታሪክ ራሱን መድገሙ አይቀሬ ይሆናል።

ትናንት አይኑን አፍጥጦ የነበረው ሌብነት በዳቦ ስሙ ሙሰኝነት ክብደት አጥቶ፤ ተግባሩም ከመጥፎ አተያይ ወደ መልካምነት ተለውጦ ዛሬም የሀገር ስጋት ሆኗል። “ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል“ የሚለው ሀገራዊ አባባልም ለችግሩ መባባስ አቅም ስለመሆኑ ለመናገር የሚከብድ አይደለም።

አባባሉ ስልጣንን የሀብት ማካበቻ አጋጣሚ አድርጎ ይወስዳል። ታዲያ ህዝብ መሪን ይፈጥራል ፤ መሪም ከህዝብ ይወለዳል! የሚል አመክንዮ ባለበት ማህበረሰብ ይህን አባባል ሰምቶ የስልጣን እርካብ የረገጠን ሹመኛ ለሌብነቱ እርሱን ብቻ ተወቃሽ ማድረጉ ተገቢ አይደለም። ህዝቡም እንደህዝብ የራሱን ድርሻ ሊወስድ ይገባል።

ወደ ዋናው ነጥባችን ስንመለስ፤በአገር አቀፍ ደረጃ ሙስናን የማጥፋት ርብርቡ ከዘመቻ ባለፈ ቀጣይነት ያለው ርምጃ ይሻል። መንግሥት በወንጀሉ ላይ ተሰማርተው በሚገኙ አካላት ላይ የሚኖረው የተጠያቂነቱ ደረጃ ከፍ ፣ ቆፍጠን ፣ ጀገን ማለት አለበት፤ ሁልጊዜ አሳዎችን ብቻ ማጥመዱ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ አይሆንም፤ ሊሆንም አይችልም።

በተጨማሪ ሙስና በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ዘርፎች ላይ ከባድ አደጋ መደቀኑን በመረዳት እያንዳንዳችን ዛሬ ላይ መከፈል ያለበትን ዋጋ ሁሉ በመክፈል መንግሥት ችግሩን ለመዋጋት የሚያደርገውን ጥረት ማገዝና ዘላቂ እልባት እንዲያገኝ መተባበር ይገባል።

አሁን እንደሚስተዋለው በዜጎች መካከል የሰማይና የምድር ልዩነት አለ። አንዱ የእለት ጉርሱ ጉዳይ ያስጨንቀዋል፤ ሌላው በሙስን እና በተጭበረበረ መንገድ ከሚፈለገው በላይ ሀብት አካብቶ ቅንጡ ኑሮ ይኖራል። ሙስና ጥቂቶችን አበልጽጎ ብዙኃኑን የሚያራቁት በመሆኑ ምስቅልቅል ማህበራዊ ሕይወት እንዲፈጠር የሚያደርግ ነው።

ከዚህ አንጻር ሙስናን መዋጋት የመንግሥት ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ማህበረሰብ ኃላፊነት መሆን አለበት። ጠንካራ ኢኮኖሚ በመገንባት ለሁሉም ዜጋ የተመቸችና የተሻለች ሀገር ለመፍጠር ሙስናን መታገል ያስፈልጋል። አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን የሚፈጽመው ሌብነት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ወላፈኑ ሁላችንንም ሊያቃጥለን ስለሚችል ከመንግሥት ጋር ቆመን ርብርብ ማድረግ ይኖርብናል ባይ ነን።

## ፋሽን

# ‹‹ዌቭ›› የወቅቱ የሴቶች የፀጉር ፋሽን

**አስናቀ ፀጋዬ**

ዘመን በተቀያየረ ቁጥር የሴቶች ፀጉር አሰራር ፋሽንም አብሮ ይቀየራል። ትናንት የነበረው ፋሽን ዛሬ የለም። ዛሬ ያለው ፋሽን ነገ አይኖርም። ነገር ግን ከብዙ ግዜ በኋላ አንዳንድ የፀጉር አሰራር ፋሽኖች ተመልሰው ሊመጡ ይችላሉ። የሴቶች የፀጉር አሰራር ፋሽን ሲባል ታዲያ ዘመናዊውንና ባህላዊውን ያጠቃልላል። ምክንያቱም በአለም አቀፍ ደረጃ አብዛኛዎቹ እንስቶች የሚከተሏቸው የፀጉር አሰራር ፋሽኖች ተመሳሳይነት ያላቸው በመሆኑ ነው።

ከዚህ ውጪ ግን ሴቶቹ እንደየሀገራቸው ሁኔታ የሚከተሏቸው ባህላዊ የፀጉር አሰራር ፋሽኖች ይኖራሉ። ለአብነትም በኢትዮጵያ ሹሩባ አንዱ ባህላዊ የሴቶች ፀጉር አሰራር ፋሽን ነው። ሹሩባ በኢትዮጵያ የገጠርም ሆነ የከተማ ሴቶች ወቅት ጠብቀው፣ በአል ተከትለው አልያም በፈለጉት ቀን መርጠው የሚሰሩት የፀጉር ፋሽን ሲሆን፤ አሁን አሁን በዘመናዊ የሴቶች የውበት ሳሎንም ጭምር በተለያየ ዲዛይን ሴቶች ይሰሩታል።

አሁን አሁን በሴቶች ዘንድ ዘመናዊን ከባህላዊ ያጣመረ የፀጉር አሰራር ፋሽን የመስራት ፍላጎት እየጨመረ የመጣ ይመስላል። ከዚህ አንፃር ዘመናዊውን የሴቶች ፀጉር አሰራር ከባህላዊ ጋር በማደባለቅ ሁሉም አይነት የፀጉር አሰራር ፋሽኖች እኔ ዘንድ አለ የሚለው አራት ኪሎ ድንቅ ስራ ህንፃ ሶስተኛ ፎቅ ላይ የሚገኘው ሃብትሽ የሴቶች የውበት ሳሎን ነው። ከፀጉር ስራ ፋሽኑ በዘለለ የእጅና የእግር ጥፍር ስራዬም የተዋጣ ነው ይላል።

ወንደሰን በቀለ የሀብትሽ የውበት ሳሎን ባለቤት ነው። በእርሱ የውበት ሳሎን በአሁኑ ጊዜ በብዙ ሴቶች ዘንድ የሚዘወተረው የፀጉር ፋሽን ‹‹ዌቭ›› ይሰኛል። ይህ የፀጉር አሰራር በሌሎች የውበት ሳሎኖችም ውስጥ ሴቶች የሚመርጡት የፀጉር ፋሽን ነው። ‹‹ዌቭ›› የሚባለው ስትሬት፣ ፐብሊሽና ስፌት ሲሆን ስፌቱ ‹‹ዌቭ›› ይሰኛል።

የ‹‹ዌቭ›› ፀጉር ስራ መጠቅለል ወይም ፀጉሩ ፍሪዝ እንዲሆን ማድረግ ሲሆን በቅድሚያ ሴቷ ፀጉሯን ታጥባና ተጠቅልላ ካስክ ውስጥ እንድትገባ ይደረጋል። ፀጉሯ ደርቆ ከካስክ ከወጣች በኋላ




**ሀብትሽ የሴቶች የውበት ሳሎን ባለቤትና የጸጉር ባለሙያው ወንደሰን በቀለ፤**

ፀጉሯ በፔስትራ ለስልሶ በካውያ ይጠቀለላል። ከዛ ፀጉሯ ሲዘረጋ ራሱ ከርል ይሆናል። ስፌት ደግሞ በፀጉሯ ላይ ሂዩማን ሄር መስፋት ሲሆን የተሰፋውን ሂዩማን ሄር በካውያ አማካኝነት ወደ ‹‹ዌቭ›› መቀየር ወይም በተለያየ መልክ ፀጉሩን መስራት ነው። ነገር ግን የአብዛኛዎቹ እንስቶች ምርጫ ዌቭ ነው።

ቀለም ሲሆን ደግሞ ገና እንዲይዝ እንደመጣች የቆሸሸው ፀጉር ላይ ከተቀባች በኋላ ትታጠብና ካስከ ትገባለች። ከካስክ ከወጣች በኋላ የምትፈልገውን የፀጉር አሰራር ትሰራለች። ነገር ግን ቀለም ከተቀባች ፀጉሯን ሁልጊዜም በተለያዩ ቅባቶችና እንደ ካስትር አይልና አልመንድ በመሳሰሉት ቅባቶች መንከባከብ የግድ ይላታል። ይህም ፀጉሯ እንዲፋፋና እንዲጠነክር ያደርገዋል።

ከ ‹‹ዌቭ›› የፀጉር ስራ በመቀጠል ሴቶች በሚፈልጉት የተለያየ ቀለሞች የፀጉር ቁርጥ ፋሽኖችን ይሰራሉ። በብዛት ሴቶቹ ለፀጉር ቁርጥ ምርጫው የሚያደርጉት ቀለም ሃይላይት ወይም ሁለት አይነት ቀለም ያለውን ነው።

ከዘመናዊው የ‹‹ዌቭ›› ፀጉር ስራ በተጨማሪ በባህላዊ መንገድ የሚሰራው አልባሶ የተሰኘው የፀጉር አሰራር በእንስቶች ዘንድ ተመራጭ የፀጉር ፋሽን ነው። በአብዛኛውም ጥምቀትን በመሰሉና በሌሎች በአላትና ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ወቅት ሴቶች ይሰሩታል። አልባሶ የሚሰራው ሹሩባው ከተሰራ በኋላ ከበስተኋላ ፍሪዝ ዊግ /የመቀሌ ዊግ/ በመስፋት ነው። ከዛም ጉብ ጉብ ብሎ በተጎነገጎነው ፀጉር ውስጥ የብረት ዱላ ይገባል። ከበስተኋላው ፍሪዝ ይሆናል። ከአልባሶ በተጨማሪ ሴቶቹ የተለያዩ ሹሩባዎችን በዊግና ያለዊግ ይሰራሉ። ቴዎድሮስና አምፖሎም ከሹሩባ ፋሽኖች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው። እነዚህም ታዲያ ወቅት ያላቸው ሲሆን ሴቶች በብዛት ክረምት ላይ ይሰሯቸዋል። ነገር ግን አሁን አሁን በበጋም ጭምር ወቅት ሳይገድበው ሴቶች የሚሰሩት ፋሽን እየሆነ መጥቷል።

ከፀጉር ስራው በተጨማሪ ሴቶች በአብዛኛው የጥፍር ሙሌት /ጄል/ ‹‹በሺላክ›› ይጠቀማሉ። ሴቶቹ እንደጣት መጠናቸው በቁጥር ጥፍር ተለጥፎላቸው ፓውደር ጄል የእግርም ሆነ የእጅ ጥፍር ላይ እንዲሞላ ይደረጋል። አንድ ጊዜ የተሰራው ጥፍር ስራም እስከ አንድ ወር ድረስ ያገለግላል። ልክ እንደ ‹‹ዌቭ›› ሁሉ የጥፍር ሙሌትም በአብዛኛዎቹ የከተማ እንስቶች ዘንድ የሚዘወተር ፋሽን ሆኗል።

ስፌት የሚሰራው በትክክለኛው ሂዩማን ሔር ከሆነ ዋጋው ከፍ ይላል። ነገር ግን በአርተፊሻል ከሆነ ይቀንሳል። አብዛኛዎቹ እንስቶች ትክክለኛውን ሂዩማን ሄር ከሌላ ቦታ ገዝተው ይዘው በመምጣት የሚሰሩ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ አርተፊሻሉን ከ500 እስከ 700 ብር ከዛው ከፀጉር ቤቱ ገዝተው ይሰራሉ።

ሀብትሽ የውበት ሳሎን በውበት ኢንዱስትሪው ሰባት አመታትን የቆየ ሲሆን፤ ደንበኞች ወደ ሳሎኑ የሚመጡት በአብዛኛው በሰው ሰው ነው። ከዚህ በተጨማሪም በኢንስታግራምና ቴሌግራም ገፅ አማካኝነት የፀጉር ስራዎችን ተመልክተው ለመስራት የሚመጡም በርካቶች ናቸው። የገበያው ሁኔታም ጥሩ የሚባል ሲሆን አምስት ሰራተኞችን ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

## ትዝብት/ ማረፊያ

# ፈር የለቀቁ የባህል ሙዚቃ ክሊፖች

**ቦጋለ አበበ**

ሰሞኑን የወጣ አንድ የሙዚቃ ቪዲዮ የበርካቶችን ቀልብ ስቧል። የሙዚቃ ክሊፑ “እናትዋ ጎንደር” ይላል። በዩቲዩብም በአጭር ጊዜ ብዙ ተመልካችና አድናቆት አግኝቷል። ሙዚቃውም ይሁን የሙዚቃው ቪዲዮ ላይ ያሉትን ቴክኒካዊ ጉዳዮች ለባለሙያዎች ወደ ጎን ትተን የተዘፈነለትን አካባቢ ቱባ ባህል ሳይበረዝ ሳይደለዝ ትክክለኛውን ገጽታ በማቅረብ ረገድ የተዋጣለት ነው ማለት ይቻላል። በእርግጥ ከዚህ የሙዚቃ ክሊፕ በፊትም በተለያዩ ጊዜዎች በበርካታ አካባቢዎች ተመሳሳይ የባህል ሙዚቃ ቪዲዮዎች በብዙ ቋንቋዎች ተሰርተው አድናቆትን አትርፈዋል። አንድ ኢትዮጵያን ቀርቶ ማንን እንደሚገልጽ ግራ የገባው የሙዚቃ ክሊፕ ለመስራት ዱባይ ባህር ዳርቻ ድረስ ብዙ ወጪ አድርገው የሚሄዱ አርቲስቶች ባሉበት በዚህ ዘመን ገጠር ድረስ ሄደው ትክክለኛውን ባህል ለማሳየት የሚጥሩ እንዲህ አይነት ባለሙያዎች ሊደነቁና ሊበረታቱ ይገባል።

የዛሬው ትዝብቴ ዘመናዊ ሙዚቃን በዘመናዊ ክሊፕ አቀረብን እያሉ እርቃናቸውን በሚባል ደረጃ እየጨፈሩ ሌትና ቀን የሚያደነቁሩን ላይ አይደለም። እነሱ አንዴ ከጥበብም ከኢትዮጵያዊ ባህልና እሴትም የተጣሉ ናቸውና ንቆ መተው እንጂ መወያያ እንዲሆኑ መፍቀድ አይገባም። ይልቁንም የሆነን ባህል ለማስተዋወቅ በሚል በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሚሰሩ የባህል ሙዚቃ ክሊፖች ላይ ትኩረት ማድረጉ የተሻለ ጥቅም አለው።

አንዳንድ ክሊፖች የተለያዩ አካባቢዎችን ባህል ለማንፀባረቅ በሚል ቢሠሩም ስህተት እንደሚበዛባቸው ማስተዋል ይቻላል። በዚህ ረገድ በተለይ በአልባሳትና ውዝዋዜ መወከል ካለባቸው አካባቢ ባህል ውጪ እንደሚሠሩ ትችት የሚቀርብባቸው ጥቂት አይደሉም። ለዚህም የሙዚቃውን ክሊፕ የሚያሰሩ አርቲስቶች ወይም ፕሮዲውሰሮች ተወዛዋዦችን በአነስተኛ ገንዘብ መቅጠር የተዋጣላቸው ክሊፖች እንዳይሠሩ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ ይነሳል። ትክክለኛውን ባህላዊ ውዝዋዜ የሚያሠለጥኑ ትምህርት ቤቶች አለመኖራቸውም ጠንካራ ሥራ እንዳይቀርብ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ ነው። ከተለመደው ወጣ ያለና ማራኪ አቀራረብ ያላቸው ክሊፖች በብዛት አለመታየታቸው ሌላኛው ችግር ሲሆን፣ ክሊፖች ተመሳሳይ እንቅስቃሴ የሚታይባቸው ለፈጠራም የታደሉ አለመሆናቸው ይታያል።

ብዙዎቹ ተወዛዋዦች ከውዝዋዜ ድረ ገጾች እያዩ ነው የሚማሩት። ከተለያዩ አገሮች የሚመለከቷቸውን ስልቶች ከባህላዊ ውዝዋዜ ጋር ደባልቀው ያቀርባሉ።ባህላዊ ውዝዋዜ ደግሞ ያለ ምንም ተጨማሪ ስልት ነው መቅረብ ያለበት።

የባህላዊ ዘፈን ክሊፖች ሲሰሩ ወደተለያዩ አካባቢዎች እየሄዱ በመመልከት የአካባቢውን ባህላዊ ውዝዋዜ በደንብ አጢኖ ማዘጋጀት ቢገባም ይህን ማድረግ በማይፈልጉና አዲስ አበባ ላይ ብቻ ተቀምጠው የተለያዩ አካባቢዎችን ባህል ለማሳየት በሚጥሩ ግለሰቦች ከባህል የሚጻረሩ ውዝዋዜዎች እየታዩ ነው።

ዘፈን ያለ ምክንያት አይዘፈንም፣ በየአካባቢው ስሜትን ለመግለጽ ወይም ለበዓላት የሚዘፈኑ ዘፈኖች የየራሳቸው አጨዋወት እንዳላቸው መታወቅ አለበት። ዛሬ ዛሬ የትኛው አለባበስና መጊያጊያጫ የቱን ብሔረሰብ እንደሚወክል ሳይታወቅ ክሊፕ ሲሠራ ይታያል።በየብሔረሰቡ ያሉ ቁሳቁሶችና አኗኗሩ መልዕክት ቢኖራቸውም ይህን ተረድተው በክሊፕ የሚያካትቷቸው ጥቂቶች ናቸው።

ከአነስተኛ ቁሳቁሶች አንስቶ የአንድ ብሔረሰብ መገለጫ የሆኑ ግብዓቶች ተሟልተው ክሊፖች መሠራት ቢኖርባቸውም የሚያሠራው ሰው በትንሽ ወጪ ለመጨረስ ሲል እንዲካተቱ ጥረት አያደርግም።ከእውቀት ማነስ በተጨማሪ ለክሊፕ የሚወጣው በጀት አነስተኛ መሆን ችግሩን ያጎላዋል።

ውዝዋዜ ፈጽሞ መነሻውን መልቀቅ እንደሌለበትና ከምንም ዘዬ ጋር መቀየጥ እንደማይገባው የዘርፉ ባለሙያዎች በአጽንኦት ሲናገሩ መስማት የተለመደ ነው። ውዝዋዜ ከሰውነት እንቅስቃሴ ባሻገር መልዕክት ማስተላለፊያ ነው።በክሊፖች ውዝዋዜ አንዳች ስሜት በሚሰጥና መልዕክት በሚያስተላልፍ መልኩ መሰናዳት ያስፈልጋል። ባህል ለማሳየትና ለክሊፑ ትርጉም ለመስጠት አስፈላጊው ወጪ ተመድቦ በጥንቃቄ ሊሰራ ይገባል።ተወዛዋዦችና ኬሮግራፈሮች የሚከፈላቸውን አስበው ድምፃውያን የፈለጉት ዓይነት ውዝዋዜ ቢያቀርቡ እንጀራ ስለሆነ ላይፈረድባቸው ይችላል። ነገር ግን ዘመናዊነት በሚል ከባህል ጋር የሚቀየጡ ውዝዋዜዎችና አልባሳት ከባለሙያዎች ተቃውሞ የሚገጥማቸው በዚህ ምክንያት ነው።

ለገበያ ሲባል ብቻ አካባቢን የማይወክሉ ሥራዎች ከሚሠሩ፣ በባለቤትነት የሚያሠሩ ድምፃውያን ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል። ክሊፖች የሚያሳድሩት ተፅዕኖ በአንዳንድ ግለሰቦች አለባበስ ላይ ጭምር መታየቱን እዚህ ጋር ማስታወስ ያስፈልጋል። ባህል እንዲጠበቅ የማድረግ ኃላፊነት ከባህልና ሚኒስቴር አንስቶ የእያንዳንዱ ሰው ኃላፊነት በመሆኑ ክሊፖች ሲሰሩ በጥናት ሊመረኮዙ ይገባል።

ክሊፖች ከተሠሩ በኋላ የሚነገርለት አካባቢ ተወላጆች ወይም ትክክለኛውን ባህል የሚያወቁ ቅሬታ ሲያቀርቡ ይደመጣሉ። አልባሳቱና ውዝዋዜው ባህሉን እንደማይገልጹ የሚተቹበትም አጋጣሚም ጥቂት አይደለም።በቸልተኝነትና የእውቀት ማነስ የሚሠሩ ስህተቶች ቢኖሩም ትክክለኛው ሥፍራ ሄዶ ለመሥራት የሚያስችል አቅም ማጣትም ለዚህ አንድ መንስኤ ነው።

ባህላዊ ክሊፖች ዘመናዊነትን ማሳየት ቢፈልጉ በዘፈቀደ ማደበላለቅ ሳይሆን ትክክለኛውን ባህላዊ ውዝዋዜ አቅርቦ ዘመናዊ የሚባለውን ለብቻው ማሳየት ይችላሉ። አቅም ያላቸውና የአንድ አካባቢን የዕለት ከዕለት ሕይወት በቅርብ ተከታትለው በክሊፖች ያካተቱ ባለሙያዎች ተደማጭነትና ተቀባይነት የሚያገኙበት ሚስጥርም ይህ ነው።

ክሊፖች ለዕይታ ከመብቃታቸው አስቀድሞ መገምገምና መታረም አለመቻላቸው ለዚህ ችግር አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ክሊፖቹ ለቀጣይ ትውልድ ባህል የሚያተላልፉና ለዓለም የሚያስተዋውቁ ከመሆናቸው አንፃር ጥንቃቄ ይጠይቃሉ። ‹‹ለምሳሌ በአማራ ክልል የጎጃም፣ ሰቆጣ፣ አገው፣ ጎንደር፣ ምንጃር፣ ከሚሴና ወሎ እየተባለ የተለያየ ጭፈራ አለ።አማራ ስለተባለ ብቻ አንድ ዓይነት አይሆንም።መጠነኛም ቢሆን ልዩነት ያላቸው እንቅስቃሴዎች ተነጣጥለው መቅረብ አለባቸው።

በክሊፖች ከውዝዋዜ በተጨማሪ የተለያዩ አካባቢዎችን አኗኗር የሚያሳዩ ክንውኖች ማካተት አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል።ለምሳሌ ስለ አፋር የተዘፈነ ክሊፕ ሲሠራ ግመልን የመሰሉ እንስሳት ወይም በአካባቢ ያለውን ልዩ አኗኗርና የሉሲን ቅሪተ አካል ማሳየት ይቻላል።ከተቻለ የአካባቢውን ተወላጆች ማሳተፍ ክሊፖቹን ከማሳመሩ በላይ ለቀጣይ ሥራዎችም ትምህርት የሚሰጥ ነው፡፡

ውዝዋዜን በትክክል ማሳየት የሰውነት እንቅስቃሴው የሚያስተላልፈውን መልዕክት ሳያዛባ ያደርሳል።የኩናማ ምት ለማስደንገጥና የጎጃም እንቅጥቅጥ ፍርኃትን ለማንፀባረቅ እንዲሁም ሌሎች ውዝዋዜዎችም መስመራቸውን ሳይለቁ ሲሠሩ ትርጉም ይሰጣሉ። በተያያዥ የትኛውም ዘፈን የሚያነሳው ርዕሰ ጉዳይ ለውዝዋዜው መሠረት መሆን አለበት።ስለ አገር፣ ፍቅር፣ ግብርና ወይም ሌላ ጽንሰ ሐሳብ ሲነሳ ክሊፑ ግጥሙን በሚገልጽ ውዝዋዜ መታጀብ አለበት፡፡

በእርግጥ በሚዘፈንለት አካባቢ የሚቀረፁ ክሊፖች ተወዳጅ የመሆን ዕድላቸው ቢሰፋም ሁልጊዜ ላይሳካ ይችላል።ክሊፖቹ በማንኛውም ቦታ ቢሠሩ በጥናት ላይ የተመረኮዙና ትክክለኛውን ባህል የሚያንፀባርቁ መሆን እንደሚገባቸው ግን ባለሙያዎች የሚያምኑበት ጉዳይ ነው። በክሊፖች ዝግጅት ድምፃውያን፣ ኬሮግራፈሮች፣ ተወዛዋዦች እንዲሁም አዘጋጆች ኃላፊነት አለባቸው። የክሊፑ ግብዓቶች ባጠቃላይ የአንድ አካባቢን ትክክለኛ ባህል የሚያሳዩ መሆን አለባቸው።

## ነፃ ሃሳብ

# ሰላም ሲሆን...

**ዳግም ከበደ**

ሰላም ለሰው ልጅ አልፋና ኦሜጋ ነው። መሸቶ እንዲነጋለት ፣ አመታት ተቆጥረው ትውልዶች መጥተው እንዲሄዱ፣ ያሰበውን ሰርቶ በሰራው እንዲረካና ከትናንቶች ዛሬን የተሻለ አድርጎ ለማለፍ ሰላም ወሳኝ ነው።

እንደ ሀገርም ሰላም ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ አድገት ወሳኝ አቅም ነው። ያለ ሰላም ሀገርን ማሰብ የዋህነት ከዛም በላይ ነው። የአንድ ሀገር ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ኢኮኖሚያዊ ሆነ ሰብአዊ ልማቶች ያለሰላም የሚታሰብ አይደለም።

ለዚህ ደግሞ በአንድ ወቅት በሰላማቸው ብቻ ሳይሆን ሰላማቸውን ተከትሎ የተሻለ ሕይወት ማሳያ የነበሩ እንደ ኢራቅ፣ ሶሪያ ፣ ሊቢያን ማየት ተገቢ ነው። እነዚህ ሀገራት ሰላማቸውን ከተነጠቁ ማግስት ጀምሮ እስከዛሬ የሀገር ወግ አጥተው የምናያቸው ሚስጢሩ ሌላ አይደለም፤ የሰላም እጦት ነው።

እነዚህ ሀገራት በእጃቸው ለነበረውና ቀደም ሲል ፈጥረውት /ተከብረው ለኖሩበት ሀገራዊ ገጽታቸው መጥፋት ዋነኛ ምክንያት የሆነውን ሰላማቸውን መጠበቅ አለመቻላቸው ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ኃላፊነት አለመፍጠራቸው ነው።

እኛም ብንሆን በተመሳሳይ መልኩ በእጃችን የነበረውን ሰላም አቅለን በማየታችን የገባንበት ጦርነት ሀገርን እንደሀገር የህልውና ስጋት ውስጥ ከትቶ እንደነበር የምንረሳው አይደለም። ይህንን ሀገራዊ ስጋት ለመቀልበስም እንደህዝብ ከፍያለ ዋጋ ለመክፈል መገደዳችንም እንዲሁ።

ዛሬ ላይ ደግሞ የጽልመት ስጋት ተገፍፎ ስለ “ሰላም” ማውራት ከጀመርን ሰነባበትን። በጦርነት እየጠፋ ስላለው ህይወት በየሰከንዱና ደቂቃው ስንጨነቅ የነበረው ጊዜ እየከሰመ ይመስላል። እጅ መጠቋቆም ትተን እጅ መጨባበጥ ላይ ደርሰናል። ስለወደመው ሳይሆን መልሰን ስለምንገነባው እየተነጋገርን ነው። ይሄ ሰላም ሲሆን የሚሰማና የሚደመጥ ትኩስ ዜና ነው።

ሰላም ሲሆን በጥላቻ መተያየትና መረጋገም ሳይሆን ስለጋራ ደህንነት፣ ስለቅንነትና መተባበር ነው የምንነጋገረው። ጥፋተኛውና በጥባጩ ማንም ይሁን ማን ላለፉት ዓመታት በሰሜኑ ክፍል ነግሶ የነበረው ውጥረት፣ ሞት፣ ውድመት በተቃራኒው ሆኖ “ኢትዮጵያ” ስለምትባል የጥንታዊ ስልጣኔ ባለቤት፣ የአኩሪ ታሪክ ሀገር ሉአላዊነትን የማስከበርና “በቅኝ አልገዛም” እምቢ ባይነት ምሳሌ ስለሆነችው ሀገራችን እየተነጋገርን ከርመናል።

ዛሬ ላይ ማንም ቢያሾልቅ ገበናችንን ያይብን የነበረውን የቤት ግድግዳችንን ሸንቁር ለመዝጋት በጋራ እየሰራን ነው። አውድማ የዋለው ገመናችን ፀሃይ እየሞቀው የነበረው ምስጢራችን ፋታ አግኝቶ በመልካም ነገር እየተካነው ነው። ይሁን እንጂ አሁንም ገና ነው። ብዙ እርቀት መጓዝ ይጠበቅብናል።

ብልሃት፣ ትእግስት፣ መተማመን እና ወንድማማችነት ትኩሱን የሰላም ዜና ለማፅናት የሚያስፈልጉ ነገሮች ናቸው። ለዚህ ደግሞ ሁለቱም አካላት በጋራ እየሰሩ እንደሆነ ከወደሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የምንሰማው መረጃ ይጠቁመናል።

ዳር ድንበሩን ለማስከበር ደፋ ቀና የሚለው የመከላከያ ሰራዊት፣ ጓዳ ጎድጓዳውን ሌት ተቀን የሚጠብቀው የፌደራል ፖሊስ ላለፉት ሶስትና አራት ዓመታት በጦርነት ታምሶ የነበረውን ቀጣና ሰላም ለማስጠበቅ እየሰሩ ይገኛሉ። ከሰላሙ ጎን ለጎን የወደሙና የተበላሹ የመሰረተ ልማቶችን ለመመለስ በመብራት ኃይል፣ በኢትዮ ቴሌኮም፤ በውሃና ፍሳሽ እና ሌሎችም ተቋማት የሚደረገው ርብርብ በእጅጉ የሚያስደንቅ ነው። ይህ የሚያሳየን ሰላም ሲሆን ሀገር እንደሚቃና፣ የጠፋው እንደሚተካ ቁስል እንደሚሽር ነው።

> አውድማ የዋለው ገመናችን ፀሃይ እየሞቀው የነበረው ምስጢራችን ፋታ አግኝቶ በመልካም ነገር እየተካነው ነው። ይሁን እንጂ አሁንም ገና ነው። ብዙ እርቀት መጓዝ ይጠበቅብናል

ሰላም ሲሆን ኢትዮጵያውያን ትንፋሽ ወስደው ኑሯቸውን ስለማሻሻል ሀገራቸውን ለማሳደግ ደፋ ቀና ስለማለት ለማሰብ ይችላሉ። መንግስት እጁ የተቀፈደደበትን ጦርነት በሰላም በመቀየሩ ዜጎች ስለሚጠቀሙበት የመሰረተ ልማት ግንባታ መጠናቀቅና አዳዲስ የልማት ግቦችን ወደ ማስቀመጥ ፊቱን እንዲያዞር ያግዛል። ከሰሞኑ የሰማነው “የፀረ ሙስና” ትግል ጅማሮ የዚህ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

“ግርግር ለሌባ ይመቻል” እንዲሉ በሰሜኑ ክፍል በተደረገ ጦርነት ምክንያት አንገታቸውን በመንግስት ጉያ ውስጥ ወሽቀው ሲዘርፉና ሲመዘብሩ የከረሙ ወንበዴዎች አሁን የሰላም ጭምጭምታ ሲሰሙ መግቢያና መውጫ እየጠበባቸው ይገኛል። መንግስትም ትንፋሽ ሲያገኝ ክፉና ደጉን ፋታ በማግኘቱ መለየት ሲችል የሀገርን ሌማት የሚቦጠቡጡ ሙሰኞች ላይ በትሩን ለመዘርጋት ሲሰናዳ ተመልክተናል። ይህ የሆነው ግጭቶችና አለመግባባቶችን በሆደ ሰፊነት ለመፍታት ስለተሞከረና ለሰላም ቅድሚያ መስጠት ስለተቻለ ነው።

ዛሬ ላይ “ይህንን ከተማ በድል ተቆጣጠርን፤ ያኛውን ተራራ ደመሰስን” ከሚል ዜና ወጥተን ሕወሓት በእጁ ያሉ ከባድ መሳሪያዎችን አስረከበ ወደሚሉ ዜናዎች ተሸጋግረናል።ይሄ የሰላም ውጤት ነው። ማንም ይሁን ማን፤ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን በሰላማዊ መንገድ ችግሮችን ለመፍታት ፍቃደኛ በመሆኑ ሊመሰገንና ሊበረታታ ይገባዋል።

ኢትዮጵያና ዜጎቿ ባለፉት አምስትና አራት ዓመታት በብዙ ጭንቅ ውስጥ አልፈዋል። ለውጡ ይዞት የመጣው ማእበል፣ ሰርተው የሚበሉ፣ አርሰው የሚያድሩ ድሆችን ህልውና ተፈታትኗል። በሰሜኑ ክፍል በተደረገው ጦርነት ንፁሃን ተገድለዋል፣ ሴቶችና ህፃናት ተፈናቅለዋል ሀብት ንብረታቸውን አጥተዋል።

በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍል አሁንም ድረስ ሉአላዊቷን ሀገር የሚፈትኑ ችግሮች እንዳሉ ቢታመንም በሰሜኑ ክፍል የሚደረገው እልህ አስጨራሽ ሀገር የማዳን ትግል ወደ ሰላማዊ መንገድ መጥቶ መረጋጋት መስፈኑ ግዙፍ ተስፋን የሚጭር ነው።

ሰላም በመሆኑ ምክንያት ለጦር መሳሪያ የሚውል ሀብት ለሀገር እና ለዜጎች እፎይታ ለሚሰጡ መሰረተ ልማት ግንባታዎች ሲውሉ ማየት ትልቅ ስኬት ነው። ሰላም መሆኑ “የጭቃ ጅራፋቸውን” የመዘዙ ህገወጥ ደላሎችን እና ነጋዴዎችን ቅስም የሰበረ ነው። ህዝቡን በጥብጠው ጥሩ ሊጠጡ የቋመጡ ቡድኖችን ሴራ የሚያከሽፍ እርምጃ ነው።

ሰላም በመሆኑ ዲፕሎማቶች ፊታቸውን የኢትዮጵያን የልማት አጀንዳዎች፣ የንግድ ስምምነት ስትራቴጂዎች፣ የሀገር ገፅታ ግንባታ ርብርብ ላይ እንዲያደርጉ እድል የሰጠ ነው። በሀገር ውስጥ ሲደረግ የነበረው የሰሜኑ ክፍል ጦርነት መቋጫ በመበሰሩ ምክንያት ባለሀብቶችና በኢንቨስትመንት መዋእለ ንዋያቸውን በኢትዮጵያ ምድር ላይ ለማድረግ ፍላጎት ያላቸው አካላት ሃሳባቸውን በድጋሚ እንዲያጤኑ የሚያግዝ እድልን የፈጠረ ነው።

አለም አቀፉ ማህበረሰብም ሰላሙን ተከትሎ የመተባበርና አብሮ የመስራት አጀንዳን ይዞ ተሰልፏል። ዜጎቻቸው ወደ ኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት፣ በቱሪዝም እና በሌሎች ምክንያቶች እንዳይመጡ እቀባና ምክረ ሃሳብ በማውጣት ተጠምደው የነበሩ ሀገራት ሃሳባቸውን ቀይረው በአዲስ ቅኝት በሀገሪቱ ስላለው ሰላምና መረጋጋት ማውራት ጀምረዋል።

የሀገሪቱን ገጽታ በተናበበ መንገድ ሲያጠለሹ የነበሩ የመገናኛ ብዙኃንም ዛሬ ከዛ መውጣት ጀምረዋል። ከዛ መንገዳቸው ተመልሰው ሀገራዊ እውነታዎችን የሚገልፁ ዘገባዎችን ዘግበዋል። ይህ ሁሉ የሆነው የውስጥ ችግሮቻችንን በሰላም ለመፍታት ባሳየነው ሆደ ሰፊነት ነው።

በኮሮና ወረርሽኝና በሀገሪቱ ልዩ ልዩ ቦታዎች በተከሰተው የሰላም መደፍረስ ምክንያት የሀገራችንን ገፅታ የምንገነባበት የቱሪዝም ኢንዱስትሪ “ጭርሱን” ሊባል በሚችል ሁኔታ ተዳክሞና ቆሞ ነበር።

ኢትዮጵያ የበርካታ ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ እንዲሁም አርኪዮሎጂካል ሀብቶች ባለቤት ብትሆንም በእነዚህ ሁለት ክስተቶች ምክንያት የውጪውም ሆነ የአገር ውስጥ ቱሪዝም ድብታ ውስጥ ገብቶ ስራ አጥነትም ሰፍኖ ነበር። ዛሬ የኮሮና ወረርሽኝ እረፍት በመስጠቱ የኢትዮጵያ መንግስት ለሰላም ስምምነቱ ሆደ ሰፊነት በማሳየቱ ምክንያት ዘርፉ ዳግም መነቃቃትና ማንሰራራት እየቻለ ነው።

ከሰሞኑ በጦርነት አውድማነት መጠቀሚያ የነበሩ የሰሜኑ ክፍል “ሰላም” በመሆኑ ምክንያት ዳግም የቀድሞ ግርማ ሞገሳቸው ተመልሶ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላትን ሲያስተናግዱ መመልከት ችለናል። ለዚህ “ገናን በላሊበላ” “ጥምቀትን በጎንደር” እና በመላው ኢትዮጵያ እጅግ ባማረና በደመቀ ኢትዮጵያዊ ስነስርዓት ተከብሮ ሲያልፍ አይተናል።

በግጭት አካባቢ የሚኖረው ሕዝባችን የጥይት ድምጽ ሳይሰማ ማደሩ ብቻ ሳይሆን ፤ ወደ ሰላማዊ ህይወቱ በመመለሱ ቀዬዎቹ ሕይወት ሕይወት መሽተት ጀምረዋል። ሕጻናት በግቢ፣ከብቶች በመስክ መቦረቅ ጀምረዋል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት “ወደ ኢትዮጵያ እንዳትመጡ” ሲሉ የነበሩ የአንዳንድ ኤምባሲዎች ማስጠንቀቂያ ቀርቶ እራሳቸው አምባሳደሮቹ በላሊበላና ጎንደር ሲምነሸነሹ ታዝበናል። ይሄ የሰላሙ ውጤት ነው ብለን በደስታ ተቀብለናል።

በጥቅሉ ሰላም ሲሆን ዜጎች እፎይታን ያገኛሉ። ጥላቻ በፍቅር ይሸነፋል። በግርግር የሚመዘብር አግበስባሽ የሚገባበት እምጥ ይጠፋዋል። በእነዚህ መልካም ነገሮች ምክንያት ሰላምን ምርጫችን ልናደርግ የግድ ይለናል።

ዛሬ የጀመርነው የሰላም ጉዞ ረጅም እርቀት እንዲሄድ የሁላችንንም ርብርብ ይሻል። በጊዜ ቆይታ እንዳንፋዘዝና እጃችን የገባውን እድል እንዳናጣ ቀናነትና ፍቅርን ገንዘባችን አድርገን በጋራ ብንሰራ መልካም ነው።

“ብረትን እንደ ጋለ ነው መቀጥቀጥ” እንደሚባለው ሁሉ ሰላማችንንም እንደያዝነው ተረባርበን እስከመጨረሻው ማስጠበቅ ይኖርብናል ፤ ስለ ሰላም የከፈልናቸው ዋጋዎች ብቻ ሳይሆኑ ላልተገባ ጦርነት የከፈልነው ዋጋ የቱን ያህል ውድ እንደሆነ በአግባቡ ልናጤን ይገባል። ሰላም!

ኢኮኖሚ

# ግብርና

## ይበልጥ መስፋፋትና መጠናከር ያለበት

# የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት



የግብርና ሜካናይዜሽን እየተስፋፋ መጥቷል

**ስምስም ምንግሥቱ**

ግብርና በኢትዮጵያ ጉርስም፣ ልብስም፣ ህልውናም ነው በሚል ይገለፃል። ይህም የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በምግብ እህል ራስን ከመቻል ባለፈ በሀገር ምጣኔ ሀብት፣ ማህበራዊ ሕይወት እድገት ውስጥ ያለውን ላቅ ያለ ሚና ያመለክታል።

በኢትዮጵያ ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ትልቁን ድርሻ ይዞ የሚገኘው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የበለጠ ተጠናክሮ ተጨባጭ ለውጥ እንዲመዘገብ በመንግሥት በኩል የግብርና ሥራውን የማዘመን ተግባር በልዩ ትኩረት መከናወኑ ቀጥሏል።

መንግስት ግብርናውን በበሬ በሞፈርና ቀንበር ከማከናወን ለመውጣት፤ በዝናብ ላይ የተመሰረተውን ግብርና በመስኖ የማጠናከር ስራ ውስጥ ገብቷል። በዚህም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የተጠናከረ ስራ እየተካሄደ ሲሆን፣ ባለፈው በጀት አመት 26 ሚሊየን ስንዴ በበጋ መስኖ ልማት ማግኘት ተችሏል።

ግብርናው በአነስተኛ የአርሶ አደሮች ማሳ ላይ ሲከናወን ነው የኖረው። ይህም ግብርናው ለዘመናዊ እርሻ ምቹ እንዳይሆን እንዳደረገው በመገንዘብ አርሶ አደሩ በኩታ ገጠም እርሻ ስራውን እንዲያከናውን እየተደረገ ይገኛል። የኩታ ገጠም ማሳ እርሻም እየተስፋፋ መጥቷል። ይህ ሁኔታም የአርሶ አደሩን ማሳ በትራክተር ለማረስ፣ ምርቱንም በኮምባይነር ለመሰብሰብ ምቹ እድል እየፈጠረ ነው።

የኩታ ገጠም እርሻ እና የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት መስፋፋት የትራክተርን፣ የውሃ መሳቢያ ሞተርንና የኮምባይነርን አስፈላጊነት የግድ እያደረጉት መጥተዋል። በአርሶ አደሮች የህብረት ስራ ማህበራትና በአንዳንድ ጠንካራ አርሶ አደሮች እጅ ብቻ የነበሩት የሜካናይዜሽን መሳሪያዎች አሁን በሌሎች የተለያዩ መንገዶች አርሶ አደሩ መንደር በስፋት የሚገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

በፌዴራል መንግስት እንዲሁም በየክልሉ ለየግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያዎች ማስፋፋት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል። የክልል መንግስታት እንዲሁም የቆላ አካባቢና መስኖ ልማት ሚኒስቴር ትራክተሮችን፣ ኮምባይነሮችንና የውሃ መሳቢያ ሞተሮችን ለአርሶ አደሮች በስፋት እያቀረቡ ናቸው። በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የመኸር እርሻ በትራክተር ሲካሄድ፣ አዝመራውም በኮምባይነር ሲከናወን የመገናኛ ብዙሃን መረጃዎች አመልክተውናል። አንዳንድ የአርሲና ባሌ አካባቢ ወረዳዎች የሜካናይዜሽን አጠቃቀም ከፍተኛ ደረጃ መድረሱንም እየተገለጸ ነው።

እነዚህን የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች ከውጭ ለሚያስገቡ ቀረጥ ነፃ አሰራር ተመቻችቷል። በሀገር ውስጥም ለአርሶ አደሮች የሜካናይዜሽን ማሽነሪ አከራዮች ማሽነሪዎችን የተወሰነ ገንዘብ ከፍለው ሌላውን ሰርተው ሊከፍሉ በሚችሉበት አግባብ በሊዝ እንዲያገኙ እየተደረገ ነው። የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለማሽነሪ አከራዮች የሜካናይዜሽን ማሽኖችን በብድር በሊዝ እያቀረበ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ባንኩ የግብርና ፕሮጀክቶችን በመደገፍና የሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት በመስጠት ለአምስት ተከታታይ ዙሮች የግብርና ሚካናይዜሽን ኪራይ አገልግሎት በመስጠት ግብርናው ላይ በተዘዋዋሪ መንገድ ድርሻ እያበረከቱ ያሉትን ተጠቃሚ አድርጓል።

የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ከማሟላት ባለፈ ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ያስገኛል ተብሎ ተስፋ የተጣለበትና ከአራት አመታት በፊት በመላ ሀገሪቱ የተጀመረው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በአብዛኛው በግብርና ሜካናይዜሽን ታግዞ እየተከናወነ ይገኛል።

በግብርና ትራንስፎርሜሽንና አረንጓዴ ኢኮኖሚ ላይ አተኩሮ የሚሰራው ‹‹ትብብር ለአረንጓዴ አብዮት በአፍሪካ›› (አግራ) የኢትዮጵያ ተወካይና የአፍሪካም ፕሮግራም መሪ ዶክተር ጥላሁን አመዴ የግብርና ሜካናይዜሽን ጉዳይ ‹‹የመፈጸም አቅም ጉዳይ ነው›› ይላሉ። የግብርና ሜካናይዜሽኑ የእርሻ ሥራውን በበሬና በትራክተር ማከናወን ብቻ እንዳልሆነም ይናገራሉ።

> በግብርና ሜካናይዜሽን በኩል የግሉን ዘርፍ ማጠናከር ውጤታማ ያደርጋል:: የማሽኑ መኖርም ብቻውን በቂ አይደለም፤ ማሽኑን ሥራ ላይ ማዋል የሚችል ብቃት ያለው የሰው ኃይል ሊኖርም ይገባል:: ይህን በሚገባ ማጠናከር ካልተቻለ ማሽኑ ያለአገልግሎት ሊቀመጥ ይችላል

እርሳቸው እንደሚሉት፤ የእርሻ ሥራ በበሬ ሲከናወን ብዙ ሀብት (ሪሶርስ) ይፈልጋል። ብዛት ያለው የሰው ኃይልና በሬ ማሰማራትንም ይጠይቃል። ይህን ለማሟላት በሚደረግ ጥረት የእርሻ ሥራው መከናወን ባለበት ጊዜ ሳይከናወን ቀርቶ ጊዜ ያልፋል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ የግብርና ሥራ በአብዛኛው ክረምትን መሠረት ያደረገ ነው። ይሄን ጊዜ በወቅቱና በአግባቡ መጠቀም ካልተቻለ ደግሞ ምርትና ምርታማነት እድገት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይደርሳል።

‹‹ዝቅተኛ ምርት ሲመረት ደግሞ ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት አስተዋጽኦ ሊኖረው ቀርቶ የምግብ ፍጆታንም ለማሟላት ያስቸግራል›› የሚሉት ዶክተር ጥላሁን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ገበሬ ምንም በሬ የሌለው፣ወይንም ደግሞ በቂ የሆነ የእርሻ በሬ የሌለው በመሆኑ በአካባቢው አንድ በሬ ካለው ጋር በማጣመር በሬ የሌለው ደግሞ በሬ ያለው አርሶ አደር የእርሻ ሥራውን እስኪጨርስ በመጠበቅ ነው እርሻውን የሚያከናውነው ሲሉ ያብራራሉ። ይህም ከመፈጸም አቅም ማነስ ጋር እንደሚያያዝም ነው የጠቆሙት።

የግብርና ሜካናይዜሽንን መተግበር እነዚህን ሁሉ ክፍተቶች ለመፍታት መልካም ጎን እንዳለው ዶክተር ጥላሁን ገልጸው፣ የተበጣጠሰ ማሳ ይዞ የግብርና ሜካናይዜሽንን ለመተግበር መነሳትም ክፍተት ስለመሆኑ ይጠቁማሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ መሬቱን ለማረስ፣ ፀረተባይ መድኃኒት ለመርጨትና ተያያዥ ተግባራትን ለማከናወን የአንዱን መሬት አልፎ ሌላኛውን በትራክተር ለማረስ በራሱ አንድ ችግር ነው። በሌላ በኩል የትራክተር አገልግሎት የሚሰጠው ኩባንያ፣ ማህበር ወይንም ግለሰብ የተለያየ ወጭ ስላለበት በእንዲህ አይነቱ መንገድ መስራት አያዋጣውም። በአጠቃላይ የተበጣጠሰ ማሳን በትራክተር ለማረስ ከምቹነትም ሆነ ከዋጋ አንጻር አዋጭ እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊያዝ እንደሚገባ ያስረዳሉ።

በአንዳንድ አካባቢዎች በግብርና ሜካናይዜሽን ጥሩ እንቅስቃሴ እንደሚታይ ጠቅሰው፣ በሌሎች ደግሞ ደካማ መሆኑን ያመለክታሉ። ችግሮች እየታዩም በአንዳንድ በባሌ አርሲ አካባቢዎች አርሶ አደሮች በጋራ ማረስና በጋራ ምርት ለመሰብሰብ ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ።

ዶክተር ጥላሁን በግብርና ሜካናይዜሽን በኩል የግሉን ዘርፍ ማጠናከር ውጤታማ እንደሚያደርግ ይጠቁማሉ። የማሽኑ መኖርም ብቻውን በቂ እንዳልሆነም ጠቅሰው፣ ማሽኑን ሥራ ላይ ማዋል የሚችል ብቃት ያለው የሰው ኃይል ሊኖር እንደሚገባም ይጠቁማሉ። ይህን በሚገባ ማጠናከር ካልተቻለ ማሽኑ ያለአገልግሎት ሊቀመጥ ይችላል ይላሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ የጥገና ስራዎችም እርሻው አቅራቢያ ሊኖሩ ይገባል። በብልሽት ከአገልግሎት ውጭ የሆነ ማሽንም በሚሰራበት ቦታ ነው የጥገና ሥራው መከናወን ያለበት። ለጥገና አገልግሎቱን ከሚሰጥበት ቦታ ወደ ሌላ ሥፍራ ለማጓጓዝ መሞከር የጊዜና የወጭ ብክነት ያስከትላል። ይሄ ደግሞ የግብርና ሥራውን ያስተጓጉላል። እነዚህ በአቅም ግንባታና በተለያየ ድጋፍ መቀረፍ ይኖርባቸዋል።

የማሽን አገልግሎት እንዲያቀርብ በሚጠበቀው በግሉ ዘርፍ በኩልም የሚሰጠው አገልግሎት በረጅም ጊዜ ጥቅም ሊያስገኝ እንደሚችል ያለው ግንዛቤም አነስተኛ መሆኑን ዶክተር ጥላሁን ያመለክታሉ። በዚህ ረገድም በረጅም ጊዜ ተጠቃሚነትን ታሳቢ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ኩባንያዎችን ለይቶና አደራጅቶ ወደ ሥራው እንዲገቡ ማድረግ እንደሚገባ አስታውቀው፣ እነዚህ ኩባንያዎች ከፍ ወዳለ ኩባንያ አድገው አገልግሎታቸውን የተሻለ እንዲያደርጉም ማበረታታት ያስፈልጋል ሲሉ ያብራራሉ።

ሜካናይዜሽን ለመሬት ለምነትና ለአካባቢ ጥበቃ ፋይዳ እንዳለውም ነው የጠቆሙት። ‹‹በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጥሩ ገበሬ ተደርጎ የሚወሰደው ደጋግሞ የሚያርስ ነው›› የሚሉት ዶክተር ጥላሁን፣ ‹‹ይሄ አላስፈላጊ ነው። አፈሩን ያበላሻል።›› ሲሉ ያስገነዝባሉ። ‹‹ደጋግሞ ማረስ መሬት ውስጥ ያለውን እርጥበት ለአደጋ ያጋልጣል፤ ብዙ ካርቦን ያለው በአፈር ውስጥ ነው። ተደጋግሞ በታረሰ ቁጥር የካርቦን አየር ተጋላጭነትን ይጨምራል።›› ሲሉ ያስገነዝባሉ።

‹‹ይሄ ደግሞ ለአካባቢ የአየር ለውጥም መፈጠርም ምክንያት ይሆናል›› በማለት ያስረዱት ዶክተር ጥላሁን፤ እነዚህን ስጋቶች መቀነስ የሚቻለው በግብርና ሜካናይዜሽን አሰራር እንደሆነ አመልክተዋል። ትራክተር ከባህላዊ ማረሻ በተሻለ ገባ ብሎ በማረስ ያለውን ችግር ያስወግዳል ብለዋል።

ዶክተር ጥላሁን እንደሚያስረዱት፣ የግብርና ሜካናይዜሽን መሬት ከማረስ፣ የደረሰ ሰብልን ከማጨድና ከመሰብሰብ ባለፈ ብዙ ጥቅሞችን የያዘ ተግባር ነው። የሜካናይዜሽን ስራ ከማምረት እስከ ገበያ የተሳሰረ ነው። ሜካናይዜሽን የኢንዱስትራላይዜሽን አካል ነው። ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ከተቻለ በኋላ ምርቱ ገበያ ላይ ውሎ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማስገኘት መቻል አለበት።

ምርቱን ጥሬውን ለገበያ በማዋል ብቻ ሳይሆን እሴት የተጨመረበት ምርትና አገልግሎት ያስፈልጋል። የተሻለ ገቢ ማግኘት የሚቻለው ምርቱን የተወሰነ ጊዜ አቆይቶ ገበያ ማውጣት ሲቻል በመሆኑ እንዲህ ያለው አሰራርም አብሮ ሊመቻች ይገባል ሲሉ ይመክራሉ።

በኢትዮጵያ ሜካናይዜሽንን ጥቅም ላይ የማዋሉ እንቅስቃሴ አንዴ ያዝ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ለቀቅ የሚደረግበት ሁኔታ ስለመኖሩ የዘርፉ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ። ይህን አስመልክቶ የተጠየቁት ዶክተር ጥላሁን፤ የደርግ አገዛዝን ይወቅሳሉ። ‹‹ የደርግ ሥርዓት በግብርናው ዘርፍ ተሰማርቶ የነበረውን የግሉን ዘርፍ ለማጥፋት ሲንቀሳቀስ ሜካናይዝድ የነበሩ እርሻዎች ተወርሰዋል። መሳሪያዎችም ባክነው ቀርተዋል›› ሲሉ ይጠቁማሉ።

የደርግ ሥርዓት ወድቆ የተተካውም የኢህአዴግ ሥርዓት የሜካናይዜሽን አገልግሎት የበለጠ እንዲዳከም አድርጓል ነው የሚሉት። ከዚህ አንጻር ሜካናይዜሽን በኢትዮጵያ አዲስ አይደለም ግን አልተጠናከረም ብሎ መውሰድ ይቻላል ይላሉ።

አሁን ደግሞ በሜካናይዜሽን ላይ የተጠናከረ ሥራ እየታየ መሆኑን ጠቅሰው፣ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ያስገነዝባሉ። ስራው የተጠናከረና ዘላቂነት እንዲኖረው ሰፊ የእርሻ መሬትና አነስተኛ የእርሻ መሬት ባለባቸው አካባቢዎች ምን እንደሚያስፈልግ መለየት፣ ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ እስከ ገቢ ሰፋ ባለ እቅድ መከናወን አለበት ሲሉ ያስገነዝባሉ።

ቅልጥፍናን የሚጨምር ነገርም አብሮ ማሰብ እንደሚያስፈልግ ነው ያመለከቱት። በአንድ ወቅት ላይ ሰብልን የሚያጠቃ ነፍሳት ተከስቶ ድሮን ጥቅም ላይ የዋለበት አጋጣሚ እንደነበር አስታውሰው፣ እንዲህ ያለውን ቴክኖሎጂ ለአንድ ወቅት ችግር ከማዋል ያለፈ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው ይላሉ።

የሜካናይዜሽን አገልግሎትን በመንግሥት ከመፈጸም በግል እንዲከናወን ማድረግ አዋጭ መሆኑን ያመለክታሉ። ለእዚህ ደግሞ ማህበራትን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ፣ መንግሥት የብድር አገልግሎትና የተለያዩ ማበረታቻዎችን ማመቻቸት እንደሚኖርበት አመልክተዋል።

ዶክተር ጥላሁን በጥሩ የግብርና ሜካናይዜሽን አጠቃቀማቸው ኬንያንና ደቡብ አፍሪካን በአብነት ይጠቅሳሉ። የሀገራቱ አርሶ አደሮች እያንዳንዳቸው ትራክተር ወይንም አጭዶ መውቂያና መሰብሰቢያ ማሽን (ኮምባይነር) እንደሌላቸውም ጠቅሰው፣ የግብርናውን ሥራ የሚያከናውኑት ግን ሜካናይዜሽን መሆኑን ጠቁመዋል።

ይህም መሆን የቻለው ጠንካራ የሆነ የሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጡ ኩባንያዎች ስላላቸው ነው ያሉት ዶክተር ጥላሁን፣ አገልግሎት ሰጭው ቀድሞ ኮንትራት ወስዶ ነው ወደ ሥራ የሚገባው ይላሉ። ኮንትራቱንም መንግሥት እንደሚያስከብር ጠቁመው፣ በዚህ መንገድ አርሶ አደሩም የሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪውም እንደሚያተርፉ ገልጸዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

## “በግልም ሆነ በመንግስት የትምህርት ተቋም የሚማሩ ተማሪዎች ዲግሪ የሚያገኙት መውጫ ፈተናውን ሲያልፉ ብቻ ነው”

**አቶ ሰይድ መሀመድ- በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና ብቃት ማሻሻያ ዴስክ ኃላፊ**

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የትምህርት ጥራት ጉዳይ እንደሀገር አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደደረሰ በተደጋጋሚ ይገለጻል። ብዙዎችም ትችት ሲያቀርቡበት ይስተዋላል። ትችታቸው ደግሞ አንድ አካል ላይ ያረፈ አይደለም። ልዩ ልዩ ምክንያቶችን ያነሳሉ። አንዱ የማስተማር ብቃት አለመኖር ሲል ሌላው የግብዓት እጥረት ነው ይላል። አንዳንዱ መነሻው ላይ ያለመስራት ችግር እንደሆነ ሲያነሳ ሌላኛው ከፍተኛ ተቋማት ተመራቂዎችን በብቃት አስተምረው ስለማያወጧቸው እንደሆነ ይጠቁማል። ሁሉም በየፊናው እየተገፋፋም ዛሬ ድረስ ችግር እንደሆነ ቀጥሏል። እናም ጉዳዩ በጥልቀት የሚመለከተው ትምህርት ሚኒስቴር ይህንን በዘርፈ ብዙ ተግባር ለመፍታት የ10 ዓመት ፍኖተ ካርታ አውጥቷል።

በየደረጃው ችግሮችን ለመፍታትም ሥራዎችን ጀምሯል። ከእነዚህ መካከል ደግሞ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ጉዳይ አንዱ ነው። ቀጣሪዎችም ሆኑ ለልምምድ የሚወጡባቸው ተቋማት በብዙ ሲማረሩባቸው ነበር። እናም ብቃት ያለው ተመራቂ ለማውጣት ዋነኛ መፍትሄው ብቃታቸውን የሚያረጋግጥ የመውጫ ፈተና መስጠት የግድ መሆኑን እንደሀገር ታምኖበታል። ለመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመውጫ ፈተናውን ለመስጠት ምን አይነት ዝግጅቶች እየተከናወኑ ነው ስንል በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና ብቃት ማሻሻያ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሰይድ መሀመድን አነጋግረናል።

**አዲስ ዘመን፡- የመውጪያ ፈተናው መሰጠት ለምን አስፈለገ ?ፋይዳውስ ምንድነው?**

**አቶ ሰይድ፡-** የመውጫ ፈተና መስጠት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ምሩቃን ገበያው የሚፈልገውን አቅምና ብቃት ያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፤ በሀገራዊ ብቻ ሳይሆን አለም አቀፋዊ ገበያው ላይ በሁሉም የትምህርት መስክ ተወዳዳሪ የሆኑ ምሩቃንን ማፍራት ስለሚያስፈልግ፤ ከሀገራዊ ኢኮኖሚው ጋር የሚዛመዱ ተማሪዎች ለማውጣት፣ ከቴክኖሎጂውና ከማህበረሰብ ፍላጎት አንጻር የሰለጠኑ እንዲሁም ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን አፍርተናል ወይ የሚለውን ለማየት ፤በእውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከት የበቁ እንዲሆኑ ለማስቻል ነው።

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው የተማሩትን ምን ያህል አውቀዋል የሚለውን ለማረጋገጥም መውጫ ፈተናው ትልቅ ፋይዳ አለው። ይህ ደግሞ የትምህርት ጥራቱን ማስጠበቂያ አንዱ መሳሪያ ነው። ስለዚህም ፋይዳው ብዙ ነው። ለምሳሌ የበቃ ተማሪ አለመፈራቱ ምሬቱን በሁሉም ደረጃ አበራክቷል። እናም በጥራትና በብቃት ተማሪዎችን የማፍራት ጉዳይ አንዱ ሆኖ ወደ ሥራ ተገብቶበታል።

በእርግጥ ይህ ሥራ አዲስ አይደለም። በአንዳንድ የትምህርት መስኮች ላይ ከዚህ በፊት ሲተገበር ቆይቷል። ብዙ ለውጥ ያመጣና ተማሪዎችን ከብቃት አንጻር ውጤታማ ያደረገም ነው። እናም የሚነሱ ክፍተቶችን ለማረም የመውጫ ፈተናው እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ታምኖበታል። ከዚህ በተጓዳኝ ተማሪው በየዓመቱ የተማረውን ትምህርት ምን ያህል አውቆት እንዳለፈ ራሱን የሚፈትሽበትና ብቁ መሆኑን የሚያረጋግጥበትም ነው። ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ባበቁት ተማሪ ልክ እውቅና የሚያገኙበት ሁኔታን ይፈጥራል።

**አዲስ ዘመን፡- የመውጫ ፈተናው ሁሉንም ትምህርቶች ያካተተ ነው ወይስ የተለየ ይዘት አለው?**

**አቶ ሰይድ፡-** በግልም ሆነ በመንግስት የትምህርት ተቋም የሚማር ተማሪ ዲግሪውን የሚያገኘው ምዘናውን ሲያልፍ ብቻ ነው። እናም ፈተናው የተማሪዎችን እውቀት፣ አመለካከትና ክህሎትን በሚለካ መልኩ የተዘጋጀ ነው። ከዚህ አንጻር ብቃትን ይለካሉ የተባሉ የትምህርት አይነቶች ( ኮርሶች) ተመርጠው ለፈተና ይቀርባሉ። የአፈታተን ዘዴው ደግሞ በበይነመረብ ሲሆን፤ መኮራረጅን ይቀንሳል ተብሎ የታሰበበት ነው። እንደየሁኔታው ማለትም እንደ የትምህርት አይነቱ የተግባር ፈተናም ይኖረዋል።

የመመረቂያ ጽሁፍ በተመለከተ በአንድ ጉዳይ ላይ ምን ያህል እውቀት እንደጨበጡ ለመለየት የሚያግዝ የምዘና ስርዓት ነው። ሁሉንም የተማርነውን በብቃት አያረጋግጥም። ስለዚህም በአሁኑ የፈተና አካሄድ ይህ አንድ መስፈርት ሆኖ ይቀጥላል እንጂ ዲግሪ የማግኛና አለማግኛ መስፈርት አይሆንም። በተመሳሳይ ለመመረቅም አያስችልም።

**አዲስ ዘመን፡- የፈተና ዝግጅቱ ምን ይመስላል፤አሁን ያለበት ሁኔታስ ?**

**አቶ ሰይድ፡-** በርካታ ቅድመ ዝግጅቶች እየተደረጉ ይገኛሉ። በመሰረተ ልማትና መሰል ነገሮች ዙሪያም የመጀመሪያ ዙር እይታ ተደርጓል። በዚህም በየዓመቱ ከ150 እስከ 180 ሺህ በመጀመሪያ ዲግሪ የሚመረቁ ተማሪዎችን ምዘና ለመስጠት የሚያስችል አቅም እንዳለ ታይቷል። ከመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት 146 ሺህ እንዲሁም ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት 110 ሺህ በድምሩ 256 ሺ ተመራቂ ተማሪዎችን የመውጫ ፈተና ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ ሰነድ ከማዘጋጀት ጀምሮ ለፈተናው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን የማሟላት ሥራ እየተሠራ ነው። ለአብነት አራት የግል ከፍተኛ ተቋማትን ጨምሮ በአጠቃላይ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችን በመውሰድ 33ሺህ የሚሆኑ ኮምፒውተሮች ዝግጁ ሆነዋል። ይህ ሲባል ደግሞ ሙሉ ግንኙነታቸው (ኮኔክሽናቸው) የተሟላና የመብራት መቆራረጥ እንዳይገጥማቸው ይደረጋል። እናም በአስር ዙር ፈተናው እንዲሰጥ ይደረግና የተፈለገውን ውጤት ለማምጣት ይሰራል።

በመንግስትና በግል ተቋማት ላይ የሚሰጡ ከ300 በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራሞች አሉ። ሁሉንም ተማሪ በአንድ ጊዜ መፈተን አይጠበቅብንምና በየትምህርት መስኩ እየተደረገ እንዲፈተኑ ይሆናል። በአንድ ቀን ውስጥ 30 የትምህርት ክፍሎችን በመፈተንም በ10 ቀን ውስጥ 300ውን ማጠናቀቅ ይቻላል በሚል ተይዟል። በዩኒቨርሲቲዎች ያለውን የኮምፒውተር አቅርቦት እና የተፈታኞች ብዛት በመለየት የመውጫ ፈተናውን በኦንላይን ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገም ይገኛል።

በየዩኒቨርሲቲዎች ለተማሪዎች አጋዥ የትምህርት ሞጁሎችን ከማዘጋጀት ጀምሮ ፈተናውን ለመውሰድ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን የማዘጋጀት ሥራ እየተሠራ ነው። ተማሪዎቻቸውን የሞዴል ፈተና እንዲሰጡም መመሪያው ያስገድዳልና ፈተናው እስኪደርስ ድረስ በዚህ መልኩ እንዲቀጥሉም እየተደረገ ነው። ያልተሟላ ነገር ካለ ደግሞ እንደ መንግስት ድጋፎች የሚደረጉ ይሆናል። በአጠቃላይ እስከ ግንቦት ወር ድረስ እንደትምህርት ሚኒስቴር ሁለት ተግባራትን ጎን ለጎን እየሰራ ነው። የመጀመሪያው ፈተናውን በተሳካ ሁኔታ ለመስጠት የሚያስችሉ ነገሮችን ማሟላት ሲሆን፤ ሁለተኛው በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉ ተማሪዎች ፈተናውን ሊሰሩበት የሚችሉበትን አቅም መፍጠር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የመውጫ ፈተናው የሙያ ብቃት ምዘና (ከሲኦሲ) ጋር ይመሳሰል ይሆን?**

**አቶ ሰይድ፡-** በፈተና ይዘታቸው ተመሳሳይነት አላቸው ተብሎ ይታሰባል። ነገር ግን አላማቸው የተለያየ ነው። የሙያ ብቃት ምዘና (ሲኦሲ) ፈተና ዲግሪያቸውን ከያዙ በኋላ ወደ ሥራ አለም ለመቀላቀል ሲባል የሚወሰድ ነው። ዝቅተኛ ብቃቱን አሟልቷል አላሟላም የሚለውን የሚመዝንም ነው። የመውጫ ፈተና ግን ከሥራው ጀምሮ የትምህርት ሴክተሩን ብቻ የሚያሳትፍ ነው። ዲግሪውን ጭምር የማግኘት ጉዳይ ነው። ብቁ ተማሪን የማፍራት እንጂ የመቀጠርን ጉዳይ አይመለከትም። ያለፉ ተማሪዎች እንደ ሲኦሲው ለመቀጠር ሳይሆን ለመመረቅ ብቻ የሚደርጉት ነው። ሥራ የመቀጠሩ ጉዳይ ከብቃት በኋላ የሚያዩት ሌላ ነገር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የመውጫ ፈተናው ዓመታትን በዩኒቨርሲቲ ቆይተው የመመረቃቸው ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ስለሚያስገባ ብዙዎች በጥርጣሬ የሚያዩት ነው። በዚህ ላይ ምን አስተያየት አልዎት?**

**አቶ ሰይድ፡-** ተማሪዎች ውጤታማ የሚሆኑትና የተሻለ አማራጭን ማግኘት የሚችሉት ብቁ ሲሆኑ ብቻ ነው። ዲግሪ ማግኘትና አለማግኘት አይደለም ግባቸው። በተማሩበት መስክ ተመርቀው ሲወጡ ምን ያህል እውቀት አላቸው? ክህሎታቸው የተሻለ እድልን ይሰጣቸዋል ወይ? የሚለው ነው ጥያቄው። ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ደግሞ ወሳኙ ነገር ፈተናውን መውሰድ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎቹን ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ያሳያልና።

ፈተናው ዲግሪ ለመስጠትና ላለመስጠት ሳይሆን የሚሰጠው ብቁ የሆነ ዜጋ ለማፍራት ነው። የዩኒቨርሲቲዎች ጉዳይ መሆን ያለበት ዜጎችን በብቃትና በእውቀት ለሀገር ማበርከት ነው። ተማሪዎችን ማብቃትን እንደ ስራ አድርጎ የሚቆጥሩ ተቋሞች መሆን አለባቸው ። ስለሆነም ጉዳዩ ከዲግሪ መስጠትና አለመስጠት ጋር ተያይዞ ሊነሳ አይገባም። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን ሲቀበሉ እናበቃችኋለን ብለው እንጂ ዲግሪ እንሰጣችኋለን አልያም ሥራ እናስቀጥራችኋለን ብለው አይደለም። እናም ሁሉም ትኩረት ሊያደርግ የሚገባው ተማሪው ብቃት ኖሮት ወደገበያው ገብቷል ወይ የሚለው ላይ ሊሆን ይገባል። ጭንቀቱም መሆን ያለበት ዲግሪ አገኛለሁ የሚለው ሳይሆን ምን ያህል ብቃት አለኝ የሚለው መሆን አለበት።



ብቃት ያለው ተማሪ ባለማፍራታችን እስከአሁን ሀገር ብዙ ዋጋ ከፍላለች። መጠቀም ያለባትን ያህልም እንዳትጠቀም ሆናለች። ለአብነት አካውንቲንግ ተምሮ ተመርቆ ቢወጣም ወደ ሥራው አለም ሲቀላቀል ግን በአግባቡ የደመወዝ መቀበያ (ፔሮል) የማይሰራ ባለዲግሪ በርካታ ነው። ስለዚህም ተማሪውም ሆነ ሌላው ማህበረሰብ ማሰብ ያለበት እንዴት ብቁ ዜጋን ማፍራት ይቻላል የሚለው ላይ ነው። በተለይ ተመራቂው ብቁ ሊያደርጉት የሚችሉት ነገሮች ላይ በመስራት የቀጣይ ራዕዩን ማሳካት አለበት። ብቁ ከሆነ ደግሞ ፈተናውን አንድ ጊዜ አይደለም ሺህ ጊዜ ቢፈተኑ እንደሚያልፈው ማመን ይጠበቅበታል። ቅጥሩም ሆነ ሌላው የግል ሥራው ፈተና እንደማይሆንበት ማሰብ አለበት። ምክንያቱም የተማረ ወድቆ አይወድቅም። በአንዱ ባይሳካለት በሌላው መሥራት ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- የመውጫ ፈተናው ለምን ያህል ጊዜ ይሰጣል፤ የወጪው ጉዳይ?**

**አቶ ሰይድ፡-** ተመራቂዎች ፈተናውን የሚወስዱት ላልተገደበ ጊዜ ነው። ዝግጁ በሆኑበት ወቅት ላይ ማሟላት ያለባቸውን ነገር አሟልተው መውሰድ ይችላሉ። ስለዚህም የተማሪው አቋማዊ ሁኔታ ብቻ ነው የሚወስነው። ይህ ሲባል ግን ልክ ትምህርቱን እንዳጠናቀቁ አይወስዱም ማለት አይደለም። ለመመረቅ ዝግጁ የሆኑትን ብቻ ሳይሆን በመጨረሻው ዓመት ላይ የሁለተኛ ሴሚስተርን እየተማሩ ያሉ ተማሪዎችንም ጭምር ባካተተ መልኩ ነው ፈተናው የሚሰጠው። ስለዚህ በመጀመሪያው ባይሳካላቸው ሁለተኛው ላይ የሚወስዱበት አጋጣሚ ይፈጠርላቸዋል።

የፈተና ወጪን በተመለከተ በመንግስት ዩኒቨርሲቲ ተምረው ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት ለመጀመሪያ ጊዜ ወጪያቸው የሚሸፍነው በመንግስት ይሆናል። በተደጋጋሚ ሲወስዱ ግን ወጪያቸውን ራሳቸው እንዲሸፍኑ መመሪያው ያዛል። ወጪው የሚወሰነው ደግሞ ወቅታዊ ሁኔታውን ባማከለ መልኩ ነው። የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በተመለከተ ከመጀመሪያው ጀምሮ በራሳቸው ወጪ እየተማሩ ስለሆነ ለፈተና የሚሆነውን ወጪም ራሳቸው ይሸፍናሉ።

**አዲስ ዘመን፡- የመውጫ ፈተናን በተመለከተ መመሪያ መውጣቱ ይታወቃል። ምን ምን ነገሮችን ያካተተ ነው?**

**አቶ ሰይድ፡-** መመሪያው ብዙ ነገሮች የተካተቱበት ነው። ከመውጫ ፈተና አስፈላጊነት ጀምሮ እስከ ተግባሪ ተቋማት ድርሻና ኃላፊነት ሙሉ ለሙሉ አስቀምጧል። ፈተናው እንዴት ይዘጋጃል፣ በእነማን፤ እንዴት ይሰጣል፤ ውጤቱ በእነማን ይለካል፤ እንዴት ይገለጻል፤ የፈተና ወጪ አሸፋፈን በምን መልኩ ይከናወናልና መሰል ነገሮችን አካቶ ይዟል። ያው በዝርዝር መመሪያዎች የሚጠናከርም ቢሆንም። ለዚህ ደግሞ ዝግጅቶች እየተጠናቀቁ ናቸው። ምክንያቱም የመተግበሪያ ዝርዝር መመሪያ ስለሚያስፈልግ።

**አዲስ ዘመን፡- በመመሪያው ላይ ሀገራዊ ዝቅተኛ የትምህርት ብቃት ብሎ ያስቀመጣቸው ነገሮች አሉ። እነዚህ ምንምን ናቸው?**

**አቶ ሰይድ፡-** በርካታ ናቸው። በየትምህርት መስኩም ተቀምጠዋል። አለያየታቸው ደግሞ በደረጃ (ሌቭሎች) የሚቀመጥ ይሆናል። ስለዚህም የትምህርት አይነቶቹ ብዙ ስለሆኑ ይህ ይህ ነው ለማለት ያስቸግራል። በጥቅሉ ግን በደረጃ እንደሚለዩ ማወቅ ተገቢ ነው። ይህንን በደንብ ለማረጋገጥ ያስችል ዘንድ በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል። ስለዚህም እርሱ ሲጸድቅ በዚያ መስፈርት መሰረት ተማሪዎች ዝቅተኛውን ብቃት አሟልተዋል አላሟሉም ተብሎ ይለያል።

**አዲስ ዘመን፡- ፈተናውን ከብልሹ አሰራር ነጻ ለማድረግ ምን ታስቧል?**

**አቶ ሰይድ፡-** የመጀመሪያው ፈተናውን በበይነመረብ ማድረግ ሲሆን፤ ይህ ደግሞ ከሰው ንክኪ ነጻ ያደርገዋል። ከሰዎች ጋር ግንኙነት ከሌለው ደግሞ ተማሪዎች በራሳቸው አቅም ሰርተው ተገቢውን ውጤት እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ተፈታኞች የራሳቸው የሚስጥር ቁጥር (ፓስወርድ) ጭምር ኖሯቸው ነው ወደፈተናው የሚገቡት። በዚህም ጎን ለጎን የሚቀመጡ የአንድ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ቢኖሩ እንኳን መኮራረጅ እንዳይችሉ ተደርጎ ነው የተሰራው።

**አዲስ ዘመን፡- የመውጫ ፈተናው ስኬታማ እንዲሆን ከማን ምን ይጠበቃል?**

**አቶ ሰይድ፡-** ከተማሪዎች ስጀምር አንድ ተማሪ ዝቅተኛ የሚጠበቅብኝ ብቃት ምንድነው? የሚለውን በደንብ ማወቅ አለበት። ለዚህ ደግሞ መነሻ የሚሆነው ሰነድ ተዘጋጅቷል። ስለዚህም ሰነዱን በደንብ በማየት በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት ይመዘናል ተብሎ የተቀመጡ መስፈርቶች አሉ፤ እነርሱን አይቶ መዘጋጀትም ያስፈልጋል። በሁለተኛ ደረጃ ብቃታቸውን ለመለየት የሚያስችሉ የትምህርት ዓይነቶች (ኮርሶችም) በመለየታቸው እነርሱን በሚገባ ማወቅና መዘጋጀት አለባቸው።

ትምህርት ተቋማትም በመመሪያው መሰረት ተማሪዎችን ብቁ ለማድረግ መስራት ይኖርባቸዋል። በተለይ በስነልቦና ሳይጨናነቁ ራሳቸውን ዝግጁ የሚያደርጉበትን ስርዓት መፍጠር ላይ በደንብ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን።**

**አቶ ሰይድ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ወቅታዊ

# «የብዝኃ ቋንቋ አተገባበር ሁሉንም ማኅበረሰብ የሚያቀራርብ ነው»

**ዶክተር ዮሴፍ ቤኮ**
**- በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ተመራማሪ**

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

በኢትዮጵያ ከ80 በላይ ቋንቋዎች እንዳሉ ይነገራል።ከእነዚህ ውስጥ የትምህርት ቋንቋ መሆን የቻሉት 53ቱ ብቻ ናቸው።ይህም ቢሆን ሥርዓት ተበጅቶለት ሳይሆን በሕገ መንግሥት የተቀመጠላቸውን መብት ለመጠቀም ጥረት ባደረጉ ማህበረሰቦች አነሳሽነት ነው። ይህም የኢትዮጵያን የብዝኃ ቋንቋ ባለቤትነትን የሚገድብ ነው።ይህንን ችግር ለመፍታትም አዲሱና ለሀገሪቱ የመጀመሪያው የሆነው የቋንቋዎች ፖሊሲ በሀገሪቱ ልሳነ ብዙኃነትን በአግባቡ ለመጠቀም፣ የሕዝቦችን የእርስ በርስ ትስስር ለማጠናከርና ቀጣናዊ ትስስርን ለማጎልበት ይረዳል ተብሎ በ10 ዓመቱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ውስጥ ተከቷል። ይህም ወደክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወርዷል። ብዙዎቹ ክልሎችም እየተገበሩት ይገኛሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግን እስከአሁን ተግባራዊ ሳያደርገው ቆይቷል። ለዚህ ዋናው ምክንያት በጥናት መመለስ ያለባቸው በርካታ ጥያቄዎች ስለነበሩ ነው።በጥናት መመለስ የሚገባቸውን ተግባራትም ለመለየት ለኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ኃላፊነት ተሰጥቶት ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ ጥናቶችን እያስጠና ሲሆን ሲጠናቀቅም ወደ ተግባር ለመግባት እየተዘጋጀ ነው። ይሄ ጥናት ምን ምን ጉዳዮችን ይዟል? ጥናቱ መቼ ይጠናቀቃል? የሚሉትንና መሰል ጥያቄዎችን በማንሳት ጥናቱን ከአደረጉት መካከል በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ተመራማሪ ዶክተር ዮሴፍ ቤኮ ጋር ቆይታ አድርገናል።

**አዲስ ዘመን፡- ብዝኃ ቋንቋ ማለት ምን ማለት ነው?**

**ዶክተር ዮሴፍ ፡-**ብዝኃ ቋንቋ ማለት በእንግሊዝኛው መልቲ ሊንጓሊዝም (Multi leagualism) ማለት ነው።ይህም አንድ ግለሰብ ከአንድ ቋንቋ በላይ ተናጋሪ ሆነ እንደማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የብዝኃ ቋንቋ ጥናት ለማድረግ አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?**

**ዶክተር ዮሴፍ ፡-** መነሻ ምክንያቶቹ በርካታ ናቸው። በዋናነት ግን ከተፈጥሯዊነት የሚመነጭ ነው።ብዙ ብሔርና ባህል ባለበት ሀገር ብዝኃ ቋንቋ ያስፈልጋል።ስለብሔር፣ ቋንቋና ባህል ስናነሳ የሚወራረሱና የሚዋዋሱ መሆናቸው እሙን ነው።እናም ይህንን የበዛ አስተሳሰብ ለማጠናከርና ለማስተሳሰር እንደ አዲስ አበባ አይነት ከተሞች እጅግ ተመራጭ ናቸው።ምክንያቱም በከተሞቹ ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች የተለያየ ባህልን የሚጋሩ፣ የአኗኗር ዘይቤዎችን የሚዋዋሱ፤በተለያየ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ መስተጋብር የተሳሰሩ ናቸው። እናም ይህንን በሚገባ ለማጠናከር ብዝኃ ቋንቋ የግድ ይሆናል።

አንደኛ ከተማዋ ባለብዙ ብሔርና ቋንቋ ተናጋሪ መገኛ መሆኗም እንዲሁ የቋንቋ ብዝኃነትን ለመተግበር እጅግ ጠቃሚ ነው። ኢትዮጵያዊያንን በትክክል የምትወክል ማንነት ያለባትና በአቀማመጧ የተነሳ ከአራቱም አቅጣጫ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የሚገቡበት አለፍ ሲልም የገበያ ምንጫቸው፣ የኑሯቸው መዳረሻ መሆኗም እርስ በርስ በቋንቋ ለማስተሳሰር ቀላል ይሆናል። እናም ሀገሪቱን ይበልጥ ለመጥቀምና የአስተሳሰብ ለውጥን ለማምጣት ሲባል የብዝኃ ቋንቋ ጥናት እንዲደረግ ተወስኗል።

በሁለተኛነት ለጥናቱ ምክንያት የሆነው ደግሞ ከተማዋ የሀገሪቱ ዋና ከተማ በመሆኗ የኢኮኖሚ ስበት ማዕከልም ናት። ይህም የብሔር ብሔረሰቦች ከተማ ያስብላታል። የከተማ ማህበረሰብ ያለባት ከተማ ብለን ልንወስዳትም እንችላለን። እናም ይህ ተፈጥሯዊ ሁኔታ ቋንቋን እንደ ትልቅ ግብዓት አድርጎ መማር ቢታከልበት የበለጠ ተጠቃሚነትን ያረጋግጣል በሚል በስርዓተ ትምህርቱ እንዲካተት በሚል የጥናቱ መነሻ ተደርጎ ተወስዷል።

ሶስተኛ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ብሔር ብሔረሰቦች ባለበት ከተማ ውስጥ አንድን ቋንቋ ብቻ የሥራና የትምህርት ቋንቋ ማድረጉ ተገቢነት





የለውም በሚል ጥናት እንዲደረግ ወስኗል።እነኝህ ሦስት አመክንዮዎችም ለጥናቱ ዋነኛ የመነሻ ሃሳብ ነበሩ።

የአደጉ አገራት ልምድ እንደሚያመላክተው የብዝኃ ቋንቋ በስርዓተ ትምህርታቸው ማካተታቸው ዜጎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጨማሪ ሌላ ቋንቋ እንዲማሩ እድል ይሰጣል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በአውሮፓ ድንጋጌ አለ። በአፍሪካ ሕብረት የአፍሪካ ፕላን ኦፍ አክሽን የሚባለው ይህንኑ ማዕቀፍን ያስቀምጣል፤ በዚህም የአፍሪካ አገራት በየትምህርት ቤቱ ተጨማሪ ቋንቋ እንዲማሩ ያስገድዳል። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የአገራችን አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ዜጎች ቢያንስ ሦስት ተጨማሪ ቋንቋዎችን መማር እንዳለባቸው ይደነግጋል። በእነዚህና መሰል ምክንያቶች ብዝኃ ቋንቋን እንደ ከተማ አስተዳደር ለመተግበር የሚያስችል ጥናት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ እንዲጠና ሆኗል።

**አዲስ ዘመን፡- ብዝኃ ብሔር ባለባት ከተማ ውስጥ ብዝኃ ቋንቋን እንዴት ማረጋገጥና ማስተማር ይቻላል?**

**ዶክተር ዮሴፍ፡-** ሳይንሱ እንደሚለው ብዙ ብሔረሰብ ባለበት አካባቢ ብዙ የቋንቋ መወራረሶች ይመጣሉ። እነዚህ ደግሞ ውበት ናቸው። አንድ አይነት መስመር ላይ መቆም አልችልም የሚሉትን እሳቤዎችም ይሰብራሉ። ምክንያቱም በጉርብትና፣ በሥራ ልውውጥ፣ በገበያውና መሰል መድረኮች ላይ ግድ ለመግባባት ሲባል አንዱ የአንዱን ቋንቋ እንዲያውቅ ይገደዳል። በሳይንስ ሲደገፍ ግን ከዚህ የተለየ ነው የሚሆነው። ብዙ ነገሮች ይካተቱበታል። ጉዳዩ ግዳጅ ሳይሆን ውዴታና ምርጫ ይሆናል። ይህ ደግሞ ይበልጥ መፈላለግን ያዳብራል።

በተለይም በትምህርት ስርዓት ውስጥ መካተቱ ተማሪው አውቆት እንዲግባባበትና የተሻለ ኑሮን እንዲመርጥበት ያደርገዋል። አንድ ኢኮኖሚ ማህበረሰብንም ለመፍጠር ሁነኛ መፍትሄ ነው። እንደሀገርም የአንድ ባህልና ማህበራዊ መስተጋብር ባለቤት የሆነ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያስችላል። ምክንያቱም በፖሊሲ ተቃኝቶ ይጓዛል።

**አዲስ ዘመን፡- ብዝኃ ቋንቋ ያለው ማህበረሰብ መፍጠር መልካም ሆኖ ሳለ በትምህርት ቋንቋ ምርጫ ምክንያት ልዩነቶች ሲፈጠሩ አይችሉም ?**

**ዶክተር ዮሴፍ፡-**ይሄ ሊፈጠር ይችላል።ልዩነቱ ሊፈጠር የሚችለው ግን ሳይንሱን ካልተከተሉ ብቻ ነው።ብዝኃ ቋንቋ እናድርግ ብሎ በዘልማድ የቋንቋ ምርጫን ማከናወን እንደማህበረሰብም ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም ችግር ይፈጥራል።

ስለዚህም የራሱ የሆነ መስፈርት አለው፤ ያንን ተከትሎ መስራት ያስፈልጋል።እነዚህ መስፈርቶች ደግሞ አራት ምሶሶዎችን ይይዛሉ።የመጀመሪያው መስፈርት ቅርበት ነው። እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከቅርበት አንጻር እንዲሁም በዙሪያዋ ካሉ ማህበረሰብ ጋር የእርስ በእርስ መስተጋብር ሲፈጥር የሚያመጣው ነገር ነው።ማህበረሰቡ በስፋት የሚናገረው ቋንቋ ምንድነው በሚለው የሚወሰድ ይሆናል።

ሁለተኛው ተደራሽነት ነው። በቅርብም ሆነ በከተማው ውስጥ በቀላሉ ተግባብተው ሊሰሩበት የሚችሉት የትኛውን ቋንቋ ቢማሩ ነው የሚለውን የሚያሳየው ነው።

ሦስተኛው የማህበረሰብ ተቀባይነትና አገልግሎት ሲሆን፤ ማህበረሰቡ የትኛውን ቋንቋ ነው የሚፈልገው፤ በቋንቋው ቢጠቀም ምን ያህል አገልግሎት ማግኘት ይችላል።እንደከተማ አስተዳደር በቀላሉ አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላል ወይ የሚለውም ይታያል።ለዚህም ግልጋሎቱና ፍላጎቱ ተጠንቶ ቋንቋው የሚመረጥበት ነው።

አራተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ተጠቃሚነትን ከማምጣት አኳያ የሚመረጥበት ነው።በኢኮኖሚ መተሳሰርን፣ በባህል መጋራትንና ማህበራዊ መስተጋብርን ያረጋግጣል ወይ ተብሎ ይታያል።በእነዚህ መስፈርቶች ቋንቋዎች ይመረጡና በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ እንዲካተቱ ይሆናል ።እናም መረጣው ሳይንሱን ከተከተለ ጥቅም እንጂ ልዩነት ወይም ግጭት አይኖርም።

**አዲስ ዘመን፡- ጥናቱ ከአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ፖሊሲ ጋር ምን ያህል የተናበበ ነው?**

**ዶክተር ዮሴፍ፡-** በሚገባ የተናበበ ነው።ምክንያቱም መነሻው እስካሁን ያለው ትግበራ ከትምህርት ስርዓቱ ጋር ስላልተናበበ ነው።ቢናበብ ኖሮ ጥናቱ አያስፈልግም ነበር።እንደ ከተማ አስተዳደር እየተተገበረ ያለው የትምህርት ስርዓት ክፍተት አለበት ።ክፍተቱ ምንድ ነው? የአለም ተሞክሮን፣ የአፍሪካንና የሀገሪቱን ተሞክሮ ሥራ ላይ አላዋለም።የሀገራችን የትምህርት ፖሊሲ በሁሉም ክልሎች ባለው አጎራባች አካባቢዎች አማርኛን ጨምሮ ሶስት ቋንቋን መማር እንደሚችሉ ያስረዳል። ነገር ግን ሌሎች ክልሎች ተግባራዊ ሲያደርጉ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተግባራዊ አላደረገውም።ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ውጪ አልተሻገረም።

ለምሳሌ፡- የኦሮሚያ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ይህንን ተግባራዊ እያደረገ ነው።ከአጎራባቾቹ ጋር የሚጋራቸውን ቋንቋዎች ሁሉ በተጨማሪነት እያስተማረ ይገኛል።ከሱማሌ፣ ከአፋር ከቤኒሻንጉል እና ከጋምቤላ ክልሎች ጋር በሚዋሰንበት ሁኔታ ላይ የአንዱን ቋንቋ ለአንዱ እየተቀያየሩ እንዲማሩ በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ አካተው ተግባራዊ እያደረጉ ነው።

በአማራ ክልል እንደዚሁ አንዳንድ ቦታዎች ተሞክሮዎቹ አሉ። ለዋቢነት አርጎብኛን፣ አገውኛና ኦሮምኛን እንደአጎራባች አካባቢዎች አንዱ የአንዱን እንዲማሩ እየተደረገ ነው።በደቡብ ክልልም በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩ ከሆነ አማርኛን ጨምረው እንዲማሩ እየተደረገ እንደሆነ መረጃዎች አሉ። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ይህንን እንዲተገብር በሚል ጥናት ወደ መስራቱ ተገብቷል። ተማሪዎችም ተጨማሪ ቋንቋ ይማሩ ዘንድ ጥናቱ እንዲደረግ ሆኗል።

ጥናት የሚነሳው ከክፍተት ነው።እናም ክፍተቱ ተጨማሪ ቋንቋ መረጣና የትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ማስገባት ሲሆን፤ ጥናቱ ያንን ለመድፈን ከባለድርሻ አካላት ጋር ተወያይቶ ለተግባራዊነቱ እየተዘጋጀ ነው።እስከታችኛው ማህበረሰብ ማለትም እስከ ተማሪ ወላጆች ወይም ቤተሰብ ድረስ በጥናቱ ላይ ውይይት ተደርጎ ሁሉም በአንድ ድምጽ በተለያዩ መድረኮች የተስማሙበትን ውጤት ይዞ ብቅ ብሏል።ብዙዎች ደስተኛ እንደሆኑበትም በጥናቱ ለማየት ተችሏል።በዚህም ከተማ አስተዳደሩ ከአዲሱ ትምህርት ስርዓት ትግበራ ጋር በብዝኃ ቋንቋ እንዲተሳሰር የማድረግ ሥራ እየተሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ጥናቱን በተመለከተ ብዥታዎች ተፈጥረዋል።ችግሮች ሲፈጠር የተነሳ ሀሳብ ነው የሚሉም አሉ፤ ይሄ ምን ያህል እውነትነት አለው፤ ጥናቱ የተጀመረው በቅርብ ነው?**

**ዶክተር ዮሴፍ፡-** በነገራችን ላይ ብዙ ሰዎች የሚያስቡት ሰሞኑን የጥናታችን ውጤት እየቀረበ እንደሆነ ነው። በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ከኦሮሚያ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር ጋር በተገናኘ ችግሮችና አለመግባባቶች ነበሩ። ከዚህ አንጻር አንዳንድ ግለሰቦች ጥናቱ የዚህን መልስ ለመስጠት የመጣ ይመስላቸዋል።በዚህም የተለያዩ አስተያየቶች ሲሰጡ ተስተውለዋል። እዚህ ላይ ሁለት ነገር መናገር እፈልጋለሁ።አንደኛው የጥናታችን ወሰኑና ጭብጡ ራሱን የቻለ ነው።በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቤቶችና ትምህርት ቢሮ አንድ ሰሞን ከተፈጠረው ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ያኛው ሌላ ጉዳይ ነው። ይሄኛው የተጨማሪ ቋንቋ ወይም ደግሞ የብዝኃ ቋንቋ የትምህርት አተገባበርን ነው። የተጨማሪ ቋንቋ ወይም ደግሞ የብዝኃ ቋንቋ የትምህርት አተገባበርን በተመለከተ የተነሳ ግጭት አዲስ አበባ ውስጥ አልሰማሁም፤ አላየሁምም።

በሁለተኛ ደረጃ ጥናቱ ከመጋቢት ጀምሮ ፕሮፖዛሉ ተቀርጾ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ማኔጅመንት ቀርቦ በየደረጃው ሲገመገም 2014 አልቆ 2015 የግብዓት መድረክ ይዘጋጃል ተብሎ አቅጣጫ ተይዞበት በዛ መሰረት የሄደ ነው። የአጋጣሚ መገጣጠም ካልሆነ በስተቀር ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር አይገናኝም። በዚህ አግባብ በተሰጠን አቅጣጫ ጥናቱን አጥንተን ተፈራርመን

# ወቅታዊ



ወደ ሥራ ገብተናል እንጂ ሌላ ተልዕኮ ኖሮት እየተሰራ ያለ ጥናት አይደለም። አሁን ወደ ፍጻሜ አካባቢ ላይ ደርሷል። ግብዓት እያሰባሰብን ነው። ይሄ ይቀጥላል። ጥናቱ ገና ግብዓት እየተሰባሰበ ነው እንጂ የተጠናቀቀ አይደለም። ገና ጥናቱ ወደ ትግበራ አልተገባበትም። ከዚህ በኋላ የሚቀጥለው ግብዓቱን አጠቃላይ አካተን የጥናታችንን ሰነድ ስናስረክብ የሚከናወን ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- የተሠራው ጥናት ከብዝኃ ቋንቋ ውጪ የያዘው ጉዳይ አለ?**

**ዶከረተር ዮሴፍ፡-** ጥናቱ ከብዝኃ ቋንቋ አተገባበር ውጭ አንድም የያዘው አጀንዳ የለም። ለምሳሌ ጥናቱ የባንዲራ የመዝሙር ጉዳይን አያካትትም። ለምን ቢባል የጥናታችን ወሰን ይሄ አይደለም። አላጠናንም በዛ ጉዳይ የሰጠነውም መፍትሄ የለም። ይሄንን የጥናታችን ጭብጥም አይመለከተውም። ጥናታችን በሌሎች የዓለም ሀገሮች በአደጉ ሀገሮች እንዲሁም በአፍሪካ ሀገራት በእኛ ሀገር ጭምር እየተተገበረ ውጤታማ የሆነ የብዝኃ ቋንቋ የትምህርት ሥርዓትን ብቻ የያዘ ነው።ይህንን ደግሞ ማህበረሰቡ በሙሉ በአንድ ድምጽ ልጆቻችን ተጨማሪ ቋንቋ መማር አለባቸው ብለው አረጋግጠውልናል። የጥናታችን ወሰን የብዝኃ ቋንቋ አተገባበር ወይም የተጨማሪ ቋንቋ አንድ የሀገር ውስጥና የውጭ ቋንቋ በተለይ የሀገር ውስጥ በአንደኛ ደረጃ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ሊተገበር የሚችል፤ የውጭ ቋንቋ ደግሞ ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ በተጨማሪ ሊተገበር የሚችል በሚል የተጠና ነው። ስለዚህም ጥናቱ ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር የሚያገናኘው የጭብጥ ግንኙነት እንደሌለው ሁሉም ሊወስደው ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- የብሔር ጽንፈኝነት ባለበት ድባብ ውስጥ ሁሉንም ማኅበረሰብ ያማከለ የብዝኃ ቋንቋ ምርጫ ማድረግ ይቻላል ወይ ፤ ይሄንን ለማስታረቅ ጥናቱ ምን አይነት መፍትሄ ይዟል?**

**ዶክተር ዮሴፍ፡-** አዎ! ይቻላል።ምክንያቱም ብሔርተኝነት በራሱ የሚጠፋው አንዱ የአንዱን ቋንቋ አውቆ መኖር ሲችል ነው።ምርጫውም ቢሆን ሳይንስን የተከተለ ስለሚሆን ያቀራርባል እንጂ አያጋጭም። ምክንያቱም በአደጉት አገራትም ሆነ ባላደጉት አገራት ይህ ተተግብሮ ብዙ ውጤቶች ታይተዋል።ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ ክልሎችም ይህ ነገር በመተግበሩ ብዙ ነገሮች ተፈተዋል።ምክንያቱም የብዝኃ ቋንቋ አተገባበር ጉዳይ ሁሉንም ማህበረሰብ የማቀራረብና ተደራሽ የማድረግ ጉዳይ ነው።

ሰው ቋንቋን የሚፈልገው ለመብት ማስከበሪያ ብቻ አይደለም። ቋንቋ ከዚህም ይልቃል።ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ባህላዊ ማንነትን ማጠንከሪያ ነው።የስልጣኔያችን ፣ የፍልስፍናችን ፣ የአኗኗራችን ፤ የእምነታች እንዲሁም የታሪካችን ጉዳይ ነው።ሁሉ ነገር በቋንቋችን ውስጥ አለ። እናም ተጨማሪ ቋንቋ መማር ባለን ላይ መጨመር ነው።ምናልባት እንኳን አሁን ካስቀመጥናቸው መስፈርቶች አኳያ ልዩነቶች ቢፈጠሩ እነዚህን የማህበረሰብ ክፍሎች በተጨማሪ ጥናት ማቀራረብ ይቻላል። ምክንያቱም በመጨመር ውስጥ መቀነስ የለምና።

በአውሮፓ አባል ሀገራት የተለያዩ ቋንቋዎች ቢኖራቸውም 20 አባል ሀገራት በሚል አንድ ሆነዋል። ሁሉም ከሁለትና ሶስት በላይ ቋንቋዎችን ተምረው ይግባቡበታል። የሚፈልጉትን ነገርም ይቀያየሩበታል። ማህበረሰባቸውን ጭምርም አቀራርበውበታል። ስለዚህም አተገባበሩ ወደ መሬት ሲወርድ የፖለቲካ መሳሪያ ካልሆነ በስተቀር መቼም ችግር አይሆንም። በጥናታችንም ያየነው በጉርብትና፤ አብሮ በመኖር ወደ ተለያየ ቦታ በመዘዋወር ሰዎች የብዝኃ ቋንቋ ባለቤት ሆነዋል።ስለዚህ ቀጣይ የሚጠይቀው ምንድነው እነዚህ ሰዎች ለሌላው እድል ነው ወይስ ችግር ነው ይህንን የተጠቀሙበት የሚል ነው።

ጥናታችን ደግሞ ይህንን መልሶታል።እንደውም እንደጥናቱ ከሆነ ዜጎች የብዝኃ ቋንቋ ባለቤት መሆናቸው አሁን ባለንበት ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ብዙ ምላሽን የሚያስገኝ ነው።ምክንያቱም አንዱ የሌላውን ቋንቋ ሲያውቅ ከእንግድነት ይልቅ ቤተሰባዊነትን፤ ከመራራቅ ይልቅ መቀራረብን፤ ከመጠራጠር ይልቅ መያያዝን እንዲመርጥ ይሆናል።ብዙ ጊዜ የማናውቀውን ነገር ነው የምንፈራው፤ የምናውቀውን ነገር በድፍረት እንናገርበታለን።

በርቀት የሚፈሩትን ነገር በቅርበት ሲያገኙት በምንም ተአምር የጥላቻ፣ የፍራቻ እንዲሁም ደግሞ የመራራቂያ ምክንያት ሊያደርጉት አይችሉም።ስለዚህ ቋንቋ ግጭት ፈጣሪ ሆኖ ሳይሆን ወቅታዊ የሀገራችን ግጭቶችና ችግሮች የሚፈጠሩት ፖለቲከኞች ለፖለቲካ ንግዳቸው ሲጠቀሙት ብቻ ነው።ከዚያ ውጪ ማህበረሰቡ ይህንን አያስበውም።ወደታች ወርደን ያየነውም ከዚህ የተለየ አይደለም።አንዱ የአንዱን ቋንቋ መማሩ ጥቅም እንዳለው ያውቃል፤ ፍላጎትም አለው።ተጨማሪ ለማወቅም ይጓጓል እንጂ መራራቂያ፣ መጋጫ አያደርገውም።

የመንግስት ፖሊሲ ደግሞ የሕዝብና የማህበረሰብ ፍላጎትን ማስከበርን ብቻ የያዘ ነው።እናም የወቅታዊ የፖለቲካ ነጋዴዎች አጀንዳ ጉዳይ ሳይሆን የህዝብ ጉዳይን ቅድሚያ ይሰጣልና በፖሊሲ ታቅፎ የሚቀራረብበትን ስርዓት ለመፍጠር ብዝኃ ቋንቋ የሁሉም ዜጋ ምርጫ እንዲሆን የማስቻል ሥራን እየሰራ ይገኛል።ኅብረተሰቡ የሚጠቀምበትን ነገር ብቻ ጉዳዩ አድርጎም ይዘልቃል የሚል ምሁራዊ አስተያየት ነው ያለኝ።

አተገባበሩ በምንም መልኩ ጫናን መሰረት ያደረገ መሆን የለበትም።በዚህ ሁኔታም እየተተገበረ አይደለም።ለዚህ ማሳያ ተግባራዊ ያደረጉ ክልሎችን ብቻ በማንሳት ማረጋገጥ ይቻላል።ግጭት ወይስ ጥቅምን አምጥቷል ስንል የኦሮሚያ ክልልን መጥቀስ በቂ ነው።የቋንቋ ብዝኃነት ከመተግበራቸው በፊት በክልሉ በተለይም ከአጎራባቾች ጋር መስማማት አልተቻለም ነበር።ለምሳሌ በኦሮሚያና ሱማሌዎች ብዙ ጊዜ ግጭት ይነሳል።አሁን ግን በክልሉ የሱማልኛ ቋንቋን መማር ሲጀመር ነገሮች ተቀይረዋል።

ሁለቱ ክልሎች በብዙ ነገሮች ተሳስረዋል።ብዙ ፋይዳ ያለው ሥራም በጋራ እያከናወኑ ነው። ዜጎቻቸውን ሰላማዊ አኗኗር እንዲኖሩ አድርገዋቸዋል።ሰላም ተፈጥሯል።ወንድማማችነት ጠንክሯል።ሕዝቦች እርስ በእርሳቸው መተባበርን መርጠዋል፤ ጀምረዋልም።በቋንቋ ጥርጣሬን ሳይሆን ጥንካሬን እናገኛለን የሚባለው ለዚህ ነው።በኢኮኖሚ መተሳሰር፣ በባህል መዋሃድ፣ በብሔር መግባባት አለ በቋንቋ።

አሁንም በጫና ሳይሆን በጥናት ላይ የተመረኮዘ የተጨማሪ ቋንቋ ትምህርት ስርዓት ትግበራ እንጂ ያለፍላጎት የሚሆን ነገር የለም።ስለዚህም ሁሉንም የብዝኃ ቋንቋ ባለቤት ለማድረግ ሁሉም በየዘርፉ እያጠና ነው።የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ይህንን ነው ያደረገው።ብዙዎች ማለትም ከአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ውጪ የሆኑ ዜጎች አማርኛን ከዚህ በፊት ሲማሩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ እያላቸው ነው።ይህ ደግሞ የግጭት መንስኤ ሳይሆን ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው መብታቸውን የሚያስከብሩበት፣ ኢኮኖሚያቸውን የሚያዳብሩበት ነው የሆነላቸው።እናም ሌሎች ቋንቋዎችን መማር በዚህ ልክ መታየት አለበት።ዝቅተኛ የሆነውን ሁለት ቋንቋ የማወቅ ልምዱን ለማዳበር በፖሊሲ ጭምር ተደግፎ ተሰጥቶናል፤ መጠቀሙ ይጠቅመናል እላለሁ እንደ ዘርፉ ባለሙያ።

**አዲስ ዘመን፡- የሌሎች አገራት ተሞክሮ ምን ይመስላል፤ በጥናቱስ ተካትቷል ?**

**ዶክተር ዮሴፍ፡-** አዎ ተካቷል።ለምሳሌ፡- ከ20 ሀገራት በላይ ያቀፈው የአውሮፓ አባል ሀገራት በብዙ ቋንቋ የተሳሰሩ ናቸው።ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ስፓኒሽ፣ ሲውዲሽ... ወዘተ። በዚህም አንዱ ከአንዱ ጋር ተግባብቶ ይኖርበታል፤ ይሰራበታልም።ለዚህ መነሻው ደግሞ አንድ ልጅ ቢያንስ ሦስት ቋንቋ እንዲናገር በትምህርት ፖሊሲያቸው ውስጥ በማስገባት እንዲማር አድርገው ይቀርጹታል።ተጨማሪ ቋንቋዎችን ያስተምሩበታል። ይህንን አድርገውም ቁጭ አላሉም። ጥናት አድረገው ተማሪዎቹ ያሉበትን ሁኔታ ተንትነዋል። ጥቅሙንም በሚገባ ተረድተውታል።ማለትም ባለብዙ ቋንቋ የሆነው ተማሪ አንድ ቋንቋ ከሚማረው ይልቅ የተሻለ ተግባቦት መኖሩን አረጋግጠዋል።

የማስታወስ ችሎታቸው እንደጨመረ፣ ለችግሮች ቶሎ መፍትሄ መስጠት የሚችሉ እንደሆኑ፤ ሥራ ፈጣሪነታቸው ፈጣንነትን የተላበሰ መሆኑን፤ ከሙያ ዘርፎች ጋር ጭምር በቀላሉ የሚግባቡ መሆናቸውን አይተውበታል።ከሁሉም በላይ የትምህርት ስኬታማነቻውን ሲለኩ ከበፊቱ በእጅጉ የላቁ እንደሆኑ አረጋግጠውበታል።እንደ አፍሪካም ቢታይ በአንዳንድ ሀገሮች ይህ እውን ሆኖ ታይቷል።ለምሳሌ፡- የሀውሳ፣ የኢጎና የሩባ ቋንቋዎች በሰፊው የአፍሪካ ሀገራት እንዲማሩ ይደረጋል።ወደ ደቡብ አፍሪካም ስንሄድ እንዲሁ አፍሪካንስ ዙቢ የሚባሉትን የመሳሰሉት ከስድስት ያላነሱ ቋንቋዎች በመማር ማስተማሩ ውስጥ ገብተው ተግባራዊ በመደረጋቸው የመጡ ለውጦች ተቃኝተዋል ። በቀላሉ ለመግባባትና ኢኮኖሚያቸውን ለማሳደግ ጭምር እየተጠቀሙበት እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ።

ዚምባቡዌም ብትሆን 17 ቋንቋዎችን ከአፍ መፍቻነት በተጨማሪ የሥራ ቋንቋ ማድረግ ችላለች።ይህ ደግሞ በብዙ መልኩ ዜጎቻቸውን ተጠቃሚ ያደረጉበት ሆኖላቸው ቀጥሏል።እንደ ሀገራችን ቢተገበር ምን ይጠቅማል ከተባለ ከላይ ለሌሎቹ የሰራው ሁሉ ለእኛም ይሰራል።በተለይም የትምህርት ጥራት ላይ ትልቅ ጥቅም እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ጥናቱ የትኛውን የማህበረሰብ ክፍል ያካተተ ነው፤ የጥናቱ ግኝትስ ምን ይመስላል?**

**ዶክተር ዮሴፍ፡-** ብዙ የማህበረሰብ ክፍሎችን አካቷል።ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ መምህራን፣ በዘርፉ የሰሩ ተመራማሪዎች፣ የቋንቋ ሊሂቃን ተሳትፈውበታል።ወደ ግኝቱ ሲገባ ደግሞ ብዙ ነገሮችን ያመላከተ ነው።እንደ ከተማ አስተዳደሩ ትምህርት የሚሰጠው በአፍ መፍቻ ቋንቋ ነው።ይህ ሲሆን ደግሞ ሰፊውን ድርሻ የሚይዘው በአማርኛ ቋንቋ የሚማረው ፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በአፋን ኦሮሞ የሚማረው ነው። ይህ ደግሞ ከብዝኃ ቋንቋ አንጻር እየተተገበረ ነው ለማለት ያስቸግራል።ምክንያቱም ትግበራው በተጨማሪ ቋንቋነት እየተከናወነ አይደለም።ስለዚህም ጥናቱ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ በተጨማሪ ተማሪዎች ምን ቢማሩ የበለጠ ተመራጭ ነው የሚለውን ለመመለስ ችሏል።

እንደ ማህበረሰቡ አሰፋፈርም ሌሎች ቋንቋዎች ምርጫ ሊሆኑ እንደሚችሉም ጥናቱ አመላክቷል። ከአፋን ኦሮሞና አማርኛ በተጨማሪ ከሀገር ውስጥ ቋንቋዎች እንደ ትግሪኛና መሰል ቋንቋዎችን ምርጫ ሊደረጉ ይችላሉ የሚል እይታንም ተመልክቷል ወሳኙ የከተማ አስተዳደሩ ቢሆንም።ምክንያቱም ተጨማሪ ቋንቋ በትምህርትነት ሲሰጥ ከፍተኛ በጀትን ይጠይቃል።ይህ ደግሞ አሁን ትምህርት ላይ እየዋሉ ካሉት ውጪ ማህበረሰቡ በትምህርት እንዲገባ የሚፈልገው ቋንቋ መኖሩን ያመላክታልና ለከተማ አስተዳደሩ እንደ እቅዱና እንዳለው በጀት እያየ ደረጃ በደረጃ ቢያካትታቸው የተባሉት ቋንቋዎች ተለይተው በጥናቱ ተቀምጠዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጥናቱን መሰረት አድርጎ ከአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ አንጻር እየተተገበረ ነው፤ ወይስ ገና ነው?**

**ዶክተር ዮሴፍ፡-** አሁን የጥናቱን ግኝት ለማህበረሰቡ እያደረስን ነው ያለነው። ግብዓት እያሰባሰብን ነው። ጥናት ከተጠናቀቀ በኋላ ሁልጊዜ ለፖሊሲ ግብዓት ሲሆን፤ ሶስት ነገር ይጠበቃል። አንዱ ጥናቱ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መጠናቱ ነው። አሁን እኛ አጥንተን ጨርሰናል። ያለቀው ጥናት ላይ ግብዓት አሰባስበን እሱን እያካተትን ነው። መጨረሻ ላይ የጥናቱን ዶክመንት ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ገቢ አድርገን የከተማው መስተዳድር በካቢኔው አጸድቆ ካመነበት ለፖሊሲ ግብዓት ያቀረብነውን ግኝት ወደ ትምህርት ሥርዓት ወይም ሥርዓተ ትምህርቱ እንደገና እንዲከለስ ያደርግበታል።

**አዲስ ዘመን፡- ጥናቱ ወደ ተግባር ከገባ በኋላ ምን ፋይዳ ይዞ ይመጣል?**

**ዶክተር ዮሴፍ፡-** የተጠናው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሆኑ በጥናቱ አዲስ አበባ የባለ ብዙ ብሔር ሀገር ትባላለች።ይህ የሚጸናው ደግሞ በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ አስገብተን ስንተገብረውና ብዙ ቋንቋ የሚነገርባት ከተማ ስትሆን ነው።በተጨማሪም ብዝኃ ቋንቋው ተግባራዊ ሲሆን፤ በመጀመሪያ ዜጎች ያለ ልዩነት ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስና የመኖር ሀብት የማፍራት እድልን እንዲያገኙ ያግዛል።ምክንቱም አንዱ የአንዱን ቋንቋ ስለሚያውቅ አይገለልም፤ ችግርም አይደርስበትም።

ሁለተኛው ዜጎች በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑና የተሻለ የገቢ ምንጭን የሚያስቡበትን እድል እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል።ምክንያቱም ምቹ ሁኔታዎችን ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው እንዲያዩና እንዲያገኙ ይሆናሉ።ሌላውና ሦስተኛው አንዱ የአንዱን ባህልና የአኗኗር ዘዬን በመጋራት አካታች የሆነ ማህበረሰብን ይፈጠራል።የማህበረሰብ ትስስርንም ያጠናክራል።መቻቻልን እንዲጎለብት አድርጎ ግጭትን ለማስወገድም ሁነኛ መፍትሄ ያገኛል።

ለዜጎች ሥራ እድል ከማግኘት አንጻር፤ ግብዓትን ከመቀያየር አኳያ፤ ጥሬ ሀብትም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በቀላሉ ለማግኘት ፈተና አይሆንበትም።አካታች የሆነ ማህበረሰብ ስለሚፈጠር።እናም የአውሮፓ ኢኮኖሚክ ኮሚኒቲ እንደሚባለው ሁሉ በብዝኃ ቋንቋ ትግበራው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ኮሚኒቲ አነስ ሲል ደግሞ የአዲስ አበባ ኢኮኖሚክ ኮሚኒቲ እንዲፈጠር ያደርጋል።ስለዚህም የጥናቱ ፋይዳ ማለቂያ የለውምና ብዙ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡*

**አዲስ ዘመን፡- ጥናቱ ቢያልቅም ለትግበራው የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ይኖራሉና ምን ምን ዝግጅቶች መደረግ አለባቸው ይላሉ ?**

**ዶክተር ዮሴፍ፡-** ጥናቱ የመጀመሪያ ድራፍት ያለቀው ሐምሌ ነው።አሁን አንዳንድ ግብዓቶችን የማካተት ሁኔታ ብቻ ነው የቀረው።የማህበረሰቡ አስተያየት ግድ ነውና የተሰበሰበውን አስተያየት በማካተት ላይ እንገኛለን።እናም በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥናቱን ላስጠናው አካል እናስገባለን።ስለሆነም እንደ ከተማ አስተዳደር ይጨመራሉ ተብለው የታሰቡ ቋንቋዎች ላይ የመጽሐፍት ዝግጅት፣ የመምህራን ስልጠናና መሰል ግብዓቶች ቀድመው መስተካከል ይኖርባቸዋል።ትልቁና ዋነኛው ተብሎ መወሰድ ያለበት ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ካሪኩለም ክለሳ ሲሆን፤ ይህንንም በማዘጋጀት በኩል ቢሰራ መልካም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**ዶክተር ዮሴፍ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## ሳኡዲዎች ከግመሎች ጋር የሚግባቡበት “ልዩ ቋንቋ” በዓለም ቅርስነት ተመዘገበ

### አልሄዳ እየተባለ የሚጠራው ልዩ ቋንቋ ከ200 አመት በላይ እድሜ እንዳለው ተገልጿል

በጋዜጣው ሪፖርተር



የሰለጠኑት “የበርሃ መርከቦች” ስማቸውንና የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ በአግባቡ መለየት ይችላሉ ተብሏል

የሳኡዲ አረቢያ ግመል አርቢዎች "ከበርሃ መርከቦቹ" ጋር የሚግባቡበትን “ልዩ ቋንቋ” ፈጥረዋል።

በግመል አርቢዎች “አልሄዳ” እየተባለ የሚጠራው ልዩ ቋንቋ ባለፈው ወር በመንግሥታቱ ድርጅት የሳይንስ እና ባህል ተቋም ዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት ተመዝግቧል ሲል አልዓይን ዘግቧል።

የሰለጠኑት ግመሎች (የበረሃ መርከቦች) የባለቤቶቻቸውን ትዕዛዝ በፍጥነት ይቀበላሉ።

በአንድ ላይ እንዲያርፉም ሆነ ማዕበል ሲመጣ አቅጣጫ እንዲቀይሩና በጥንቃቄ እንዲንቀሳቀሱ አሳዳጊዎቻቸው የሚሰጧቸውን መመሪያም ለመተግበር አይቸገሩም።

በበርሃ ለረጅም ሰዓት ያለ ውሃ ጥም የሚጓዙት ግመሎች በሳኡዲ አረቢያ፣ የአረብ ኢምሬትስ እና ኦማን ሁነኛ የትራንስፖርት አማራጭ ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው።

ይህም ግመሎች ላይ ያተኮሩ ፕሮጀክቶች በስፋት እንዲካሄዱ እና የግመል ማርባት ስራም በስፋት እንዲካሄድ አድርጓል።

ሳኡዲዎች ከትውልድ ትውልድ ያስተላለፉት ግመሎችን የሚያነጋግሩበት ቋንቋም በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብ ሲጠየቅ ቆይተዋል።

ሳኡዲ፣ ኤምሬትስ እና ኦማን በጋራ ያደረጉት ጥረትም ባለፈው ወር በመንግሥታቱ ድርጅት የሳይንስ እና ባህል ተቋም ዩኔስኮ ምላሽ አግኝቶ “አልሄዳ” በዓለም ቅርስነት ተመዝግቧል።

ልዩ ቋንቋው ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውል ሲሆን፥ እያንዳንዱ ግመሎች በአሳዳጊዎቻቸው የተሰጣቸውን ስም ይለያሉ ተብሏል።

“ግመሎቹ የአሳዳጊዎቻቸውን ድምጽ ለይተው ምላሽ ይሰጣሉ፤ ሌሎች ሰዎች ሲጠሯቸው ግን አይሰሙም” ይላሉ ሃማድ አል ማሪ የተባሉ ከ100 በላይ ግመሎች ያሏቸው ግለሰብ።

የተራራቁ ግመሎችን በአንድ መንጋ እንዲጓዙ በማድረግ ከአውሎ ንፋስ ለመጠበቅም ይሄው ቋንቋ አገልግሎት ላይ እንደሚውል ነው የሚናገሩት።

አሰልጣኞቹ ግመሎቹ ቀኝ እና ግራን እንዲለዩ፣ አፋቸውን እንዲከፍቱ እና ሽብረክ ብለው እንዲያርፉ እንደሚያለማምዱም መንሱር አል ቁቱላ የተሰኙት የአልሄዳ ቋንቋ አሰልጣኝ ይገልጻሉ።

ይህን እውቀትም ከአያትና አባታቸው መቅሰማቸውን ነው ለቲ አር ቲ ወርልድ የተናገሩት።

ከ200 አመት በላይ እድሜ እንዳስቆጠረ የሚነገርለት “አልሄዳ” በዩኔስኮ መመዝገቡ ቋንቋው እንዲጠበቅና እንዲስፋፋ ያግዛል ተብሏል።



ፕሬዚዳንት ኤርዶሃን ከዩክሬን አቻቸው ጋር በስልክ ተወያይተዋል

## የቱርክ ፕሬዚዳንት ሩሲያና ዩክሬንን ለማደራደር በድጋሚ ጥያቄ አቀረቡ

### ቱርክ፣ ዩክሬን እና ሩሲያን የማደራደር ሚና ስትወጣ መቆየቷ ይታወቃል

በጋዜጣው ሪፖርተር

የቱርክ ፕሬዚዳንት ረሲፕ ጣኢብ ኤርዶሃን ሩሲያና ዩክሬንን ለማደራደር በድጋሚ ጥያቄ አቀረቡ ሲል ቢቢሲና ሬውተርስ ዘገቡ፡፡

ኤርዶሃን ጥያቄውን ያቀረቡት የዩክሬኑ አቻቸው ፕሬዚዳንት ቮሎዲሚር ዘለንስኪ ጋር በስልክ ባደረጉት ውይይት መሆኑን ሬውተርስ ዘግቧል፡፡

የሩሲያንና የዩክሬንን መሪዎች በአካል የማገናኘት ፍላጎት እንዳላቸው በተለያዩ ጊዜያት ሲገልጹ የሚደመጡት የቱርኩ ፕሬዚዳንት ረሲፕ ጣኢብ ኤርዶሃን፤ አገራቱ ወደ ተኩስ አቁም እንዲገቡና ሰብዓዊ እርዳታ ያለገደብ እንዲተላለፍ የጀመሩት የማደራደር ሂደት ውጤት እያሳየ መምጣቱ ይታወቃል፡፡

ቱርክ ባደረገችው ጥረት የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲተላለፍ መደረጉም አይዘነጋም፡፡

ይሁንና ደም አፋሳሹን የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት በዘላቂነት ለመፍታት የአገራቱ መሪዎች ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት መምጣት ወሳኝ እንደሆነ ኤርዶሃን በጥብቅ የሚያምኑት ጉዳይ ነው ሲል ሬውተርስ ዘግቧል፡፡

አዳዲስ ክስተቶች እያስተናገደና እየተወሳሰበ የመጣው የዩክሬን ጦርነት መፍትሄ ካልተበጀለት ከባድ ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችል በርካቶች ስጋታቸውን ያነሳሉ፡፡

አሁን ላይ ወደ ዩክሬን እየጎረፈ ያለው የጦር መሳሪያ ሞስኮ የከፋ እርምጃዎች ለመውሰድ ሊያስገድዳት እንደሚችል እየተነገረ ነው፡፡

በምዕራባውን ድርጊት የተበሳጨችው ሩሲያ የዩክሬን አጋሮች ከድርጊታቸው ካልተቆተቡ "ዩክሬን ሙሉ በሙሉ መጥፋቷ አይቀሬ ነው" በማለት በማስጠንቀቅ ላይ ትገኛለች፡፡

የሩሲያ የደህንነት ምክር ቤት ምክትል ኃላፊ ዲሚትሪ ሜድቬዴቭ፤ ሩሲያ በዩክሬን ከተሸነፈች ያሏትን የኒውክሌር አረር እንደምትጠቀም በቅርቡ መዛታቸውም አይዘነጋም፡፡

ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ

የአንድን ሀገር እድገትና ብልጽግና ለማረጋገጥ፣ በዜጎች መካከል ያለ እምነት እና መልካም ግንኙነት ለማዳበር እንዲሁም የሕግ የበላይነትንና መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ ትምህርትና ሥልጠና ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ ከዚህ መርህ አኳያ ትምህርትና ሥልጠናን ከልማት ጋር በማስተሳሰር የሀገራችንን እድገት ለማፋጠን እንዲቻል የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በ1986 ዓ.ም ተቀርጾ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል። በዚህ ፖሊሲ መሠረት ባለፉት ሃያ ስምንት አመታት በየአምስት ዓመቱ የተከፋፈሉ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብሮች ሀገሪቱ ቃል ከገባችባቸው የትምህርት ለሁሉምና የምዕተ ዓመቱ ልማት ግቦች ጋር በማስተሳሰር ሲተገበሩ ቆይተዋል።በመሆኑም በዛሬው እትማችን የትምህርት ሥልጠና ረቂቅ ፖሊሲ ምን ጉዳዮችን እንዳካተተ ክፍል አንድን አዘጋጅተን አቅርበናል፡፡

ትምህርትና ሥልጠና በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በማስፋፋት የትምህርትን ተደራሽነት ማሳደግ ተችሏል። በዚህም ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰው ኃይል በማቅረብ አስተዋጽኦ ያደረገ ቢሆንም በሚፈለገው ጥራት እና አይነት ከማቅረብ አንጻር ክፍተቶች ነበሩበት። በተጨማሪም ሥርዓተ ትምህርቱም ተግባር ተኮር ባለመሆኑ ሥራ ፈጣሪ የሆኑ ዜጎችን ከማፍራት፣ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራዎችን ከማበረታታት አንጻር እንዲሁም ሀገር በቀል ዕውቀቶችን በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ አካቶ ተግባራዊ በማድረግ ሀገራዊ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አኳያ ሰፊ ክፍተቶች ታይተዋል።

ስለሆነም ፖሊሲው ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች፣ እጥረቶች እንዲሁም የዘርፉን አለማቀፋዊ ለውጦችን መሰረት በማድረግ ፖሊሲውን ማሻሻል አስፈልጓል። ይህ ፖሊሲ የትምህርትና ሥልጠና ዘርፉ ያለበትን ደረጃ በመገምገም የዘርፉን ዋና ዋና ችግሮችና የፖሊሲ ማነቆዎች በፖሊሲው የሚፈቱበትን አግባብና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲው ተፈጻሚ ሲሆን የሚጠበቁ ቁልፍ ውጤቶችን በሚያሳይ መልክ የተዘጋጀ ነው።

**የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መነሻዎች**

ትምህርትና ሥልጠናን ከልማት ጋር በማስተሳሰር የሀገራችንን እድገት ለማፋጠን እንዲቻል የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በ1986 ዓ.ም. ተቀርጾ ሲተገበር ቆይቷል። ቢሆንም እድሜያቸው ለትምህርት ደርሶ አሁንም ትምህርት ያልጀመሩ ሕጻናት መኖር፣ የትምህርት ውስጣዊ ብቃት ችግሮች እንዲሁም ልዩ ፍላጎት ያላቸው በተለይም የአካል ጉዳተኞችና የጐልማሶች የትምህርት ተሳትፎ መጠን ዝቅተኛ ነው። የትምህርት ጥራትም እያሽቆለቆለ የመጣ ሲሆን እንደ ማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችለው በየደረጃው ያለው አብዛኛው ተማሪ የትምህርት ውጤት በፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን 50 በመቶና በላይ ውጤት ማምጣት አልቻለም፡፡ ሥርዓተ ትምህርቱም በንድፈ ሃሳብ የታጨቀ፣ ለነባራዊ የሀገሪቱ ሁኔታዎች ምላሽ የማይሰጥ፣ የሀገር በቀል እውቀትን ያላካተተ፣ በየጊዜው የማይፈተሽ፣ ዜጐችን በግብረ ገብና በመልካም ሥነ ምግባር በበቂ ሁኔታ ያላነፀ ከመሆኑም በላይ ለሥራ ፈጣሪነትና ለዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት የሚያዘጋጅ አልነበረም፡፡

መምህራን ብቃትን ተላብሰው ተማሪዎችን በመረዳትና በመርዳት እንዲሁም ከሚፈለገው የብቃት ደረጃ ላይ በማድረስ ረገድ ውስንነት ያለባቸው ሲሆን ትምህርት ቤቶችም ቢሆኑ ለመማር ምቹ ያልሆኑ፣ አስፈላጊው ግብዓት ያልተሟላላቸውና ትምህርቱንም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አስደግፈው የሚሰጡ አይደሉም፡፡ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማቅረብ አኳያ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ በዓለም ደረጃ ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎች ተቀምረውና ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ስትራቴጂ ወጥቶ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከፖሊሲ፣ ከስትራቴጂ፣ ከአደረጃጀትና ከአሠራር፣ ከአተገባበር እንዲሁም ከፋይናንስ ጋር በተያያዙ ችግሮች ምክንያት ኢኮኖሚውን በተለይም ግብርናውን ማዘመን አልተቻለም፡፡ ከስትራቴጂ አንጻር ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ተደራሽነት ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የሥልጠና ተቋማት አልተደራጁም፡፡

ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ መሠረት ለሆነው ለእርሻና ግብርና ትኩረት ያልሰጠና ይህንን አዘምኖ ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር ሊደግፍ አልቻለም፡፡ የተለያዩ የኢንዱስትሪና የኢኮኖሚ ዘርፎች ተቀናጅተው ለዘርፋቸው ተገቢ ብቃትና ክህሎት ያላቸውን የመካከለኛ ደረጃ ባለሙያዎች የሚያሰለጥኑበት ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡ሀገራዊ ፍላጎትን በትክክል ያገናዘበ የሙያ ደረጃ በማውጣትና የትብብር ሥልጠናን መተግበር የሚያስችል ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ በማድረግ ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነትን በማስፋት በኩል ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ተቋማት የሚፈለገውን ስታንደርድ ያልጠበቁና ብዙ መሠረተ ልማት ያልተሟላላቸው መሆኑ በትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ ጥራትና አግባብነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ፣ ኢኮኖሚው ሳይፈቅድ በ70/30(ሰባ ሰላሳ) ቀመር ላይ የተመሠረተውን የሣይንስና የማህበራዊ ሣይንስ የትምህርትና ሥልጠና ምጥጥን መተግበሩ፣ በተግባር የተደገፈ ትምህርት አለመሰጠቱና ጠንካራ የሆነ የጥራትና አግባብነት ተቆጣጣሪ ባለመኖሩም ጥራቱንና አግባብነቱን ማስጠበቅ አልተቻልም። በሌላ በኩል ሲታይ ለጥራት ወሳኝ የሆኑ የጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት ሕብረተሰቡን ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ውስነቶች ተስተውሏል። በአጠቃላይ ሲታይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ከኢንዱስትሪው ጋር የተሳሰረና የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ትምህርትና ሥልጠና እውን ማድረግ አልቻለም።

ከትምህርት አመራር አንፃር ስንመለከተው ከፌዴራል እስከ ትምህርት ቤት ድረስ ያለው አብዛኛው በየደረጃው ያለው የትምህርት መዋቅር የትምህርት አመራርና ባለሙያ ኃላፊነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የጐደለው በመሆኑ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱን በአግባቡ በመምራት ለተሻለ ውጤት ያበቃ አልነበረም፡፡ ለዚህም ሙያዊ አቅም ያላቸውን በውድድር አለመመደብና ውጤታማነት የጐደለው የሥልጠና ሥርዓት ጥራት እያሽቆለቆለ እንዲመጣ አንዱ ምክንያት ሆኗል።

በተጨማሪም መንግስት ባለፉት ዓመታት የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋት ከፍተኛ የሆነ ሀብትን በመመደብ የዘርፉ ዋነኛ የፋይናንስ ምንጭ ነበር። ይህ ተደራሽነትን በማስፋፋት በኩል አውንታዊ ሚና የነበረው ቢሆንም በከፍተኛ ትምህርትና በአጠቃላይ የትምህርት ዘርፍ ፋይናንስ ላይ ተጽእኖ ፈጥሯል። በመሆኑም በቀጣይ አማራጭ የገቢ ምንጮችን እንዲሁም ፋይናንስ አደራረግ ሥርዓት ማስፈን ያስፈልጋል።

ዩኒቨርሲቲዎች የሚያፈሩትን የሰው ሀይል ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችላቸው የአካባቢያቸው ፀጋን መሰረት ያደረገ ሥልጠና ላይ ሲሰማሩ እንደሆነ ቢታመንም በሀገሪቱ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች ሁሉንም የትምህርት አይነት መክፈት ለዚህም ከፍተኛ የሆነ ሀብት ለመሰረተ ልማት ግንባታ እና ለመማር ማስተማር በመመደብ የሀብት ብክነት እያስከተሉ ይገኛሉ። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲዎች ያላቸውን የተፈጥሮ ፀጋንና የተሰጣቸውን ጥራት ያለው የሰው ሀይል የማፍራት ተልዕኮ መሰረት ያደረገ ለመሰረተ ልማት ማስፋፋት እንዲሁም ለመማር ማስተማር ተግባራቸው ማስፈፀሚያ የሚውል የሀብት አመዳደብ ሥርዓት ሊበጅ ይገባዋል።በመሆኑም አሁን እየተተገበረ ያለውን የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በመፈተሽ በሁሉም ዘርፎችና ደረጃዎች ለሚታዩት ነባራዊ ሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጥና ተወዳዳሪ ዜጋ ለመፍጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ይገባል፡፡

# ስፖርት



# የክለቦች ዓመታዊ በጀት በአማካኝ አንድ ቢሊየን ብር ደርሷል

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያን እግር ኳስ ጠንቅቀው የሚያውቁ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ «በሀገሪቷ ቡድን እንጂ ክለብ የለም» ሲሉ ይሰማል። ምክንያቱ ደግሞ በዓለም አቀፍ የስፖርት ተቋማትም ሆነ በሀገሪቷ የስፖርት ፖሊሲ መስፈርትን የሚያሟሉ ክለቦች ባለመኖራቸው ነው። በእርግጥ እንደ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ስፖርት ላለማደጉ በዋናነት ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል አንዱ የአደረጃጀት ችግር መሆኑ ይታወቃል። ይህ ሁኔታ በተለይ የሚስተዋለው እንደ እግር ኳስ ባሉ ስፖርቶች ሲሆን፤ ክለቦች አሁንም ድረስ ራሳቸውን የመቻል ጥረት ሲያደርጉ አይታይም ።



በመሆኑም እጅግ ከፍተኛ የሚባል ገንዘብ አሁንም ድረስ ከመንግስት ካዝና ወጥቶ ስፖርቱ ይፈሳል። ይህም ለህዝብ ሊሟሉ የሚገባቸው በርካታ መሰረተ ልማቶች እያሉ በዚህ ደረጃ ስፖርቱ ላይ መዋእለ ንዋይ መፍሰሱ ተገቢ አይደለም በሚል ለትችቶች በር ከፍቷል። የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ አክሲዮን ማህበር በቅርቡ ባስጠናው ጥናት ይህንን ያረጋገጠ ሲሆን፤ በፕሪምየር ሊጉ የሚጫወቱት 16 ክለቦች (ከሁለቱ በስተቀር ሁሉም የመንግስት ናቸው) በቢሊየን የሚቆጠር ገንዘብ በየዓመቱ ፈሰስ ይደረግባቸዋል። ከዚህ ውስጥ 70 ከመቶው የሚውለው ደግሞ ለተጫዋቾች ደመወዝ ነው። ለአንድ ዓመት ከመንፈቅ የተካሄደውን ጥናት የመሩት ዶክተር ጋሻው አብዛ በገለጻቸው ወቅት ይህንኑ አስገንዝበዋል።

የጥናቱ ግኝት እንደሚያመላክተው ከሆነ አንድ የሊግ ክለብ በአማካይ ለተጫዋቾች ደመወዝ ብቻ 40ሚሊየን ብር ያወጣል። ይኸውም በክለቡ ከሚታቀፉት 25 ተጫዋቾች ቢባዛ በዓመት አንድ ክለብ 1ነጥብ6 ሚሊየን ብር ወጪ ያደርጋል ማለት ነው። ይህ ቁጥር ሲሰላም አንድ ተጫዋች በወር የሚያገኘው ደመወዝ 133ሺ334 ብር ወይም 2ሺ667ዶላር (1ዶላር በ50 ብር ቢተመን) ይደርሳል። ይኸው በአፍሪካ ካሉ የሊግ ክፍያዎች በጥቂቶቹ ተበልጦ ከምስራቅ አፍሪካ በቀዳሚነት እንዲቀመጥ ያስችለዋል። ደመወዝን ጨምሮ በአጠቃላይ የሊጉ ክለቦች ዓመታዊ በጀት ሲደማመርም እስከ 1ቢሊየን ብር ይደርሳል። በመሆኑም ልማትን ያማከለ የደመወዝ ክፍያ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግም ነው በጥናቱ ምክረ ሃሳብ የተመላከተው።

ይህ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብም የሚመደበው ከመንግስት ካዝና በመሆኑ፤ በጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ አካላት ይህ የገንዘብ ምንጭ ዘላቂነትና ተጠያቂነትን በተላበሰ መልኩ መስመር መያዝ እንደሚገባውም ነው የገለጹት። ይኸውም ሊሆን የሚችለው ክለቦቹ ራሳቸውን ለመቻል ጥረት ካደረጉ አሊያም የተጫዋቾች የደመወዝ ጣሪያ ሲወሰን ነው። ነገር ግን በኢትዮጵያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ይህንን ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም። ጥናቱ በቀረበበት መድረክ ተሳታፊ የሚመለከታቸው አካላትም ክፍያው በጥናቱ ላይ ከተገለጸውም እንደሚልቅ ጠቁመዋል። በመሆኑም ክፍያን በሚመለከት የህግ ማዕቀፍ እንዲሁም ሀገር በቀል የተጫዋቾች ክፍያና ዝውውር ስርዓት ማበጀት ተገቢ ነው። በተጨማሪም መንግስት ላወጣው ወጪ ኦዲት ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን አክሲዮን ማህበሩም የክለቦቹን ገቢና ወጪ የመፈተሽ ኃላፊነት እንዳለበት ተጠቁሟል።

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ ከተሳታፊዎች የተነሳው ሃሳብም የተጫዋቾች ክፍያ ሊጋነን የቻለው የሊጉ ክለቦች ወጣት ተጫዋቾችን በማሳደግ ሳይሆን በዝውውር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ነው። በወኪሎችና በደላሎች የሚከናወነው አግባብ ያልሆነ አሰራር ንረቱን ከማምጣት ባለፈ ገንዘቡ በትክክል ተጫዋቾች ጋር ስለመድረሱም አጠራጣሪ ሁኔታዎች አሉ። ስፖርቱን በበላይነት የሚመራው ፌዴሬሽንም ቢሆን የካፍ መመሪያዎችን በትክክል እየተገበረ አይደለም። በመሆኑም ጥናቱ እንዲሁም የሊጉ አክሲዮን ማህበር እነዚህን ጉዳዮች በተጨማሪነት እንዲያጤናቸው አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ አክሲዮን ማህበር የቦርድ ሰብሳቢ መቶአለቃ ፈቃደ ማሞ፤ የፋይናንስ ችግር የክለቦችን ህልውናን ከሚፈትኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ መሆኑን ገልጸው፤ ክለቦች ከመንግስት በሚያገኙት ድጎማ ይቀጥላሉ ወይስ መጠነኛ ገቢ በማመንጨት ህዝባዊ ይሆናሉ የሚለው ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን አብራርተዋል። መቶ አለቃ ፍቃደ አክለው እንደገለጹት፣ ክለቦች ራሳቸውን የማይችሉ ከሆነም ላለፉት ዓመታት ሲንገዳገድ የቆየው እግር ኳስ በነበረበት ይቀጥላል። በመሆኑም ራሳቸውን የሚችሉና ገቢ የሚያመነጩ ክለቦች ማቋቋም አስፈላጊ ነው፤ ለዚህም መሰል ጥናቶች ከፍተኛ ሚና አላቸው። ካልሆነ ግን በቅርብ ጊዜ ውስጥ የስፖርት ቤተሰቡ የሚመኘውን የዓለም አቀፍ ውድድሮች ተሳትፎ ቀርቶ በሀገር ውስጥ ውድድሮች የሚኖራቸው ተሳትፎም ጥያቄ ውስጥ የሚገባበት እድል ሰፊ ነው። በመሆኑም አክሲዮን ማህበሩ ባስጠናው ጥናት ላይ ባለድርሻ አካላቱ የሰጡትን አስተያየት እንደ ግብዓት በማካተት ስትራቴጂክ እቅድ አዘጋጅቶ በቅርቡ ወደ ተግባር ለመግባት ጥረት እንደሚያደርግ የቦርድ ሰብሳቢው አረጋግጠዋል።


## ሲዳማ ክልል

የባለብረቱ ስም አሠራር አወል የተሽከርካሪ ዓይነት ት/ሣ የሠሌዳ ቁጥር 1ደህ 01922 የፊት/የኋላ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ2/5/2015 ዓ.ም አልክተዋል። ስለዚህ ሠሌዳው ወድቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሪፖርት እንዲያደረግ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**ሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርትና መንገድ ልማት መምሪያ**

## አማራ ክልል

ንብረትነቱ አሊ ሁሴን የሆነ ባጃጅ ተሽከርካሪ ሰሌዳ ኮድ 01-52057 አማ ሰሌዳ የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በቀን 19/04/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም ሰሌዳውን ወድቆ፣ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአብክመ ትራንስፖርት ሎጀስቲክ ባለሥልጣን የደ/ወሎ ዞን ትራ/ተጠሪ ጽ/ቤት**

## ኦሮሚያ ክልል

ንብረትነቱ ጃማል ዲባ ስም የተመዘገበ ኮድ ኦሮ የሰሌዳ 3-44622 ኦሮ የኋላ ሰሌዳ የጠፋ ለመሆኑ በ21/04/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡ በዚሁ መሠረት ሰሌዳውን ወድቆ፣ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**ኦሮሚያ የክልላዊ መንግሥት የቦረና ዞን ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

የባለንብረቱ ስም በአቶ ቦረና ሁንዴሳ የሰሌዳ ቁጥር 2-A18098 ኦሮ ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በቀን 01/05/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ሰሌዳውን ወድቆ፣ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የአዳማ ከተማ ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ አቶ ሚሊዮን ገብረየስ ደምሴ እና በተከሳሽ ወ/ሮ አይናለም ታደሰ ታምሩ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ ወ/ሮ አይናለም ታደሰ ታምሩ በ06/06/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀነ ቀጠሮ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መናገሻ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ሁሴን አሊ ሐሠን የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01 B07214 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር AHTBB3CD301768054 ሞዴል GUN125L-DNTHXW የሞተር ቁጥር 2GD-0785458 የሊብሬ ቁጥር 238567 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የፊት ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 2/5/2015 ቀን በተጻፈ ማመልከቻ ምትክ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ስለሆነም ምትኩን ከመስጠታችን በፊት እንዲመዘገብና በእናንተ በኩል የማይፈለግ ስለመሆኑ ተጣርቶ እንዲገለጽልን እንጠይቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ለገሠ አዱኛ ኤጀርሳ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-34088 የተሽከርካሪዉ አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር 1628092 ሞዴል 504 GL የሞተር ቁጥር 1628092 የሊብሬ ቁጥር 288455/583720/311097 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 3/5/2015 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሰለሞን ታደሰ ወ/ጎርግስ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-46556 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር WJME3TRS40C242491ሞዴል AT380T38H የሞተር ቁጥር F3BEE681G*B219-161507* የሊብሬ ቁጥር 0089568/0233306 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 19/4/2015 አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ኮልፌ ቀራኒዮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ባለንብረት ስም ደስታ ካሴ ብዙነህ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-95825 የተሽከርካሪው አይነት ፈሳሽ ጭነት የሻሲ ቁጥር LZZ5BLSF5HA179855 ሞዴል ZZ1257N4347N1 የሞተር ቁጥር WD615.47*170107018867* የሊብሬ ቁጥር 0192669 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 2/5/2015 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ደስታ ካሴ ብዙነህ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-A11806 የተሽከርካሪዉ አይነት ፈሳሽ ጭነት የሻንሲ ቁጥር LZZ5BLSf2MN889055 ሞዴል ZZ1257S4341W የሞተር ቁጥር WD615472105070561 27 የሊብሬ ቁጥር 0257360 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 2/5/2015 አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዛኦድ ተሾመ አበበ ሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-06236 የተከርካሪ አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር JAMTFR52HPE-7102682 ሞዴል TFR 52 የሞተር ቁጥር 997437 የሊብሬ ቁጥር 429843 ከላይ የተቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 4/5/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን አመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ካህሱ ገ/ዚሔር ገ/ስላሴ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B57040 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር NZE120-3123579 ሞዴል CBA-NZE121-AEPNK የሞተር ቁጥር 2NZ-4203764 የሊብሬ ቁጥር 163625 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 3/5/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ኮልፌ ቀራኒዮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**